*Ethiop.j.lang.cult.com.mun.2024, 9(2): 287-319* *Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*Open Access Licensed under Creative Commons:* *ISSN: 2518-2919*
*CC BY-NC-ND 4.0*
DOI 10.20372/ejlcc.v9i2.1915

**Original Research**

# የዋሽንት ተጫዋቹ ዮሐንስ አፈወርቅ ሙያዊ አበርክቶ

**Firehiwot Bayu**

Addis Ababa University, Academy of Ethiopian Languages and Cultures,
Addis Ababa, Ethiopia

* *Corresponding author: firebayu@gmail.com*

## Abstract

This study focuses on the autobiography of Yohannis Afework, especially the part about playing the flute. The focus of this study is on how to develop experience in flute playing. The study obtained its input information from interviews and documents. The method of the study is based on the method of oral history research that applies the method of interview and document inspection. The results show that Yohannes Afework started playing the flute in their hometown (Gojam) when they were children. After coming to Addis Ababa in 1955 (E.C.), he started entertaining the village children and was employed in the then-popular dance halls as well as various traditional musical instrument-playing institutions and theaters. He has accompanied the music of various famous Ethiopian singers with flute. He is remembered by most of the people for his flute music, which is the soundtrack of the “Fikir eske mekabir.” Yohannes Afework, who lived for half a century as a flute player, even though they retired (1995 E.C.), they never stopped playing the flute. Yohannis Afework passed away on February 19, 2011 (E.C.).

ይህ ጥናት የዮሐንስ አፈወርቅ ግለታሪክ በተለይ ዋሽንት ጨዋታን በሚመለከተው ላይ ያተኮረ ነው። የመጠናቱ ዋና አላማ ዮሐንስ አፈወርቅ የዋሽንት ጨዋታ ሙያን ከለመዳ ጀምሮ እውቅ ባለሙያ እስከ መሆን የደረሱበትን ባህላዊ ዳራ ማሳየት ነው። ለጥናቱ ግብአት የሆነው መረጃ ከባለታሪኩ በቃለመጠይቅ እንዲሁም ከሰነዶች የተገኘ ነው። የአጠናን ስልቱም የቃላዊ ታሪክ ጥናት የቃለመጠይቅ እና የሰነድ ፍተሻ ዘዴን የሚተገብርበትን ስልት የተከተለ ነው። የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ዮሐንስ አፈወርቅ በህጻንነት እድሜያቸው በትውልድ አካባቢያቸው (ጎጃም) በእረኝነት ላይ እያሉ ጀመሩ። በ1955 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ የሰፈር ልጆችን ከማዝናናት ጀምሮ በወቅቱ ታዋቂ በነበሩ ጠጅ ቤቶች እንዲሁም በተለያዩ የባህል ሙዚቃ መሳሪያ አጫዋቾች ተቋማት፣ ትያትር ቤቶች ተቀጥረው ሰርተዋል። የተለያዩ ታዋቂ የኢትዮጵያ ዘፋኞችን ሙዚቃ በዋሽንት አጅበዋል። ዋሽንት ለመጫወት ኢትዮጵያን ወክለው ከሀያ በላይ የዓለም ሀገራትን ዞረዋል። በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ የፍቅር እስከመቃብር ትረካ ማጀቢያ በሆነው የዋሽንት ዜማ ይታወሳሉ። ለግማሽ ምእተ አመት ገደማ በዋሽንት ሙያ ተሰማርተው የኖሩት ዮሐንስ አፈወርቅ በ1995ዓ.ም. ጡረታ ቢወጡም በተገኘው አጋጣሚ ከዋሽንት ጨዋታ አልተለዩም። ለሙዚቃ ሙያ ቅርበት ያላቸው እንዲሁም የዋሽንትን ሙዚቃ የሚጫወቱ ባለሙያዎች ዮሐንስ አፈወርቅን የዋሽንቱ ንጉስ ሲሉ የሙያ ብቃታቸውን መስክረውላቸዋል። ዮሐንስ አፈወርቅ የካቲት 19 2011ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። በጥቅሉ ዮሐንስ አፈወርቅ በኢትዮጵያ ሀገር በቀል እውቀት ለመዳ ዘዴን ተከትለው የዋሽንት ጨዋታን እውቅ ባለሙያ ሆነዋል። ለሙያው ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት ህዝብ ከሚሰበሰብበት የሰፈር አደባባይ ጀምሮ በታሪክ ከተመዘገቡ ዓለም አቀፍ መድረኮች ድረስ ተጫውተዋል። የአድማጭ ተመልካቹ ምላሽ ሙያውን መተዳደሪያ አድርገው ከህጻንነት እድሜ እስከ ሽምግልና ከዋሽንት ሳይለዩ የኢትዮጵያን የዋሽንት አጨዋወት በኖሩበት ዘመን አሻራቸው ጎልቶ እንዲታይ አድርገዋል።

**ቁልፍ ቃላት፤** ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ትውፊታዊ የሙዚቃ መሳሪያ፣ ዋሽንት

**Citation:** Firehiwot Bayu. (2024). የዋሽንት ተጫዋቹ ዮሐንስ አፈወርቅ ሙያዊ አበርክቶ. *Ethiopian. Journal of Language, Culture and Communication, 9*(2). 287-319. DOI 10.20372/ejlcc.v9i2.1915

| *Submitted: September 2024* | *Revised: November 2024* | *Acceptted: December 2024* |
|---|---|---|

# መግቢያ

ክትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል አንዱ ዋሽንት ነው። "በተለያዩ ሀገሮች አገልግሎት የሚሰጡ የሙዚቃ መሳሪያዎች በርካታ ቢሆኑም በትንፋሽ፣በግጭት፣ በንዝረት እንዲሁም በኤሌትሪክ ድምጽ የሚሰጡ ተብለው ይከፈላሉ። በሀገራችን ከኤሌትሪክ መሳሪያዎች በቀር ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱ አይነት በብዛት ይገኛሉ"። የኢትዮጵያን የሙዚቃ መሳሪያዎች በተለይም ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ...የትንፋሽ፣ የክር፣ የአጀብና የምት መሳሪያዎች በማለት የሚመድቧቸውም አሉ (ተስፋዬ, 2005, p.66; Zenbe, 1987, p.68)።

ዋሽንት ውስጡ ክፍት ከሆነ ቀርከሃ ወይም ሸንበቆ የሚሰራ አራትና ከዚያ በላይ ብሶች ያሉት ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው(የአማርኛ መዝገበቃላት, 2006)። የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ከከብት እና ከአራዊት ቀንድ፣ ከእጽዋት በተለይ ከሸንበቆና ከቀርከሃ ይዘጋጃል። ዋሽንት የሚሰራው ከሸንበቆ ሲሆን፣ ከጎኑ አራት ቀዳዳዎች ይኖሩታል። ቀዳዳዎቹ የተመጣጠነ ርቀት ሲኖራቸው ከላይ ያሉትን ሁለት፣ የታችኞቹን ሁለት ቀዳዳዎች በሸንበቆው አንጓ ይከፈላል። በአራቱ ቀዳዳዎች ትይዩ አራት የእጅ ጣቶች እንቅስቃሴ በማድረግ የተለያየ ድምጽ ያወጣል። ዋሽንት የተለያየ ቅጥነትና ውፍረት፣ ርዝመትና እጥረት ባላቸው ሸንበቆዎች የሚሰራ ነው። ወፈር ያለው ዋሽንት ወፈር ያለ ድምጽ ሲያወጣ ቀጠን ያለው ዋሽንት ደግሞ ቀጠን ያለ ድምጽ ይኖረዋል (ተስፋዬ, 2005)::

ዋሽንት የሀዘንና የደስታ መግለጫ ጥንታዊ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን በአብዛኛው እረኞች በሀገር ቤት እራሳቸውን ለማዝናናት ይገለገሉበታል። በኢትዮጵያ ከሚገኙ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች ራሱን ችሎ ዜማዎችን ለመጫወት ከሚያስችሉት አንዱ ዋሽንት ነው። ሆኖም የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎች በህብረት መስራት ከጀመሩ ወዲህ ዋሽንት አገልግሎቱ ሰፍቶ የተለያዩ ጣእመ ዜማዎችን የሚያዜሙበት፤ እንዲሁም ለክራርና ለመሰንቆ ቅኝት በመስጠትና ዜማን በማጀብ እያገለገለ ይገኛል። ዋሽንት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በስፋት የሚታወቅ የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ስያሜውም

እንደየቋንቋው የተለያየ ነው። ለምሳሌ በጻውሮ ዋሽንት "ሱሱሊያ" በመባል ይታወቃል (ተስፋዬ, 2005, p.74; አድማሱ, 2008, p.54)::

የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፤ ሰኔ 7/2009 ዓ.ም. በባህር ዳር ዩንቨርሲቲ አባይ የባህልና ልማት ጥናት እና ምርምር ማእከል ሶስተኛውን ሀገር አቀፍ የአዝማሪ ዐውደ ጥናት ሲያካሂድ በጉባኤው ላይ ከተጋበዙት መካከል አንዱ ዮሐንስ አፈወርቅ ነበሩ። ዮሐንስ አፈወርቅ በጉባኤው መክፈቻ ዕለት ተጋብዘው የፍቅር እስከመቃብርን (የወጋየሁ ንጋቱን) ትረካ ያጀበውን የዋሽንት ዜማ አሰሙ፤ ሲጨርሱ አጠገቤ ተቀመጡ። መነሻ የሆነኝ ወጋየሁ ንጋቱ ፍቅር እስከ መቃብርን ሲተርክ የሚያጅበውን የዋሽንት ዜማ ደጋግሜ የሰማሁት ቢሆንም ባለሙያውን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋቸው መሆኔ ነው። እኚህን ባለሙያ ባለማወቄ የዋሽንት ጨዋታ ሙያን በተለይም የዮሐንስ አፈወርቅን በተመለከተ "የተጻፈ መረጃ፣ የተጠና ጥናት" ካለ በሚል በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የሚገኙ ቤተ መጻህፍት እና በተለያዩ ድረ ገጾች ላይ ፈልጌ አላገኘሁም። በተጨማሪም በቅርብ የሚያውቋቸውን ግለሰቦች ጠየኩ፤ ሆኖም በባለዋሽንቱ ዮሐንስ አፈወርቅ ግለታሪክ ላይ የተጻፈ መረጃም ሆነ የተጠና ጥናት ስለመኖሩ እንደማያውቁ ነገሩኝ። በዚሁ ምክንያት "አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ በሙያቸው ያቆዩትን አሻራ መዝግቦ ማቆየት ተገቢ ነው" ብዬ ስላመንኩ ይህንን ጥናት ለማጥናት መነሻ ምክንያት ሆኖኛል። መጠናቱም ለባህላዊ የኢትዮጵያ ሙዚቃ፣ እንዲሁም በዋሽንት ተጫዋቹ ሙያዊ አበርክቶ የተመለከተውን ግለታሪካቸውን፣ ማጥናት፣ መሰነድ አስፈላጊ በመሆኑ ይህን ክፍተት ለመሙላት ጥናቱ ተከናውኗል።

የአቶ ዮሐንስን የዋሽንት ጨዋታ ሙያ በተመለከተ ለማጥናት ወስኜ ፈቃዳቸውን ጠይቄ ይሁንታ በማግኘት በተለያየ ጊዜ ቃለ-መጠይቅ አድርጌላቸው ነበር፤ ሆኖም ሳልጨርሰው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። በሞታቸው ሰሞን የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን ሞታቸውን ምክንያት በማድረግ ዘግበዋል በጋዜጣ የወጡ ጽሁፎም ነበሩ። እነዚህም ለዚህ ጥናት ግብአት ሆነዋል። ሆኖም በተደራጀ መልኩ የተጠና ጥናት የለም። ስለዚህ ይህ ጥናት መጠናቱ ያባለሙያውን አበርክቶ ለመሰነድ ያስችላል።

የጥናቱ ዋና አላማ የዮሐንስ አፈወርቅን ዋሽንት ጨዋታ የሚመለከተውን የህይወት ታሪክ መሰነድ ነው። የጥናቱ ዝርዝር

አላማዎች፤ የዮሐንስ አፈወርቅ የዋሽንት ሙዚቃ ለመዳን አጋጣሚዎች መጠቀም፣ ዮሐንስ አፈወርቅ በዋሽንት ሙያ ያበረከቱትን ሙያዊ አበርክቶ ማሳየት ናቸው። የጥናቱ ጠቀሜታ፤ ሀገር በቀል እውቀት በተለይ ዋሽንት ለሙዚቃው መስክ ያለውን አስተዋጽዎ ማሳያ ይሆናል። ባህሉ ለሙዚቃው ምን አወንታዊና አሉታዊ መልኮች እንደነበሩት በዮሐንስ አፈወርቅ ከግማሽ ምእተ አመት በላይ ጉዞ ለኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ የራሱ አስተዋጽዎ ይኖረዋል። እግረ መንገድም እንደባለሙያ የህይወት ታሪካቸው ይዘከርበታል። በተጨማሪም ያልሰራነውን ለመስራት የሰራነውን ለማጎልበት የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል። ጥናቱ በዋነኝነት በቃለመጠይቅ በተጨማሪም በሰነድ ምርመራ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ላይ የተመሠረተ ነው። ቃለመጠይቁ ቀደም ሲል ባለታሪክ ከሆኑት ዮሐንስ አፈወርቅ እና ከቅርብ ወዳጆቻቸው ጋር በአጥኚዋ የተደረገ ነው። ስለባለታሪኩ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲሁም ሙያውንና ዘመኑን አስመልክቶ በልዩ ልዩ ቅርጽ ለተለያየ አላማ ከተጻፉ መጻህፍት፣ መጣጥፎች፣ ጋዜጦች፣ መጽሄቶች፣ እንዲሁም በድምጽና በምስል፣ በሬድዮና በድህረ ገጾች የተገኙ መረጃዎች ለዚህ ጥናት ዋቢ በመሆን አገልግለዋል።

## የጽንሰ ሀሳብ ዳራ

የዚህ ጥናት ጽንሰ ሀሳባዊ ማህቀፍ የፎክሎር አጥኚዎች ቃላዊ ታሪክን የሚያጠኑበት ስልት ነው። ስልቱም የታሪኩ ባለቤት የሆኑትን፣ መረጃ ሰጪ በማድረግ እንዲሁም ስለሚጻፈው ታሪክ አብረው ኖረው፣ ሰርተው ወይም በቅርበት የታሪኩ አካል የነበሩትን በቃላዊ ታሪክ የቃለመጠይቅ አጠያየቅ ዘዴ በመጠየቅ የሚደራጅ መረጃ ማለት ነው። ቃላዊ ታሪክ እውቅና አግኝቶ እንደ አንድ የጥናት መስክ ተጠናክሮ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው በ1960ዎቹ አካባቢ ነው። የቃላዊ ታሪክ ዋንኛ ጠቀሜታ ታሪኩ ህይወት እንዲኖረው ማድረግ ነው። ይህም የግለሰቦችን ግለ ታሪክ በመረዳት በግለታሪካቸው ውስጥ የኖሩበትን ዘመን ሁነት ለመገንዘብ ያስችላል። እንዲሁም ባለፈው ጊዜ ውስጥ የተከወኑትን የተለያዩ ጥበባዊ

ክዋኔዎች ማሳያ ነው። በዚህ ጥናትም ዮሐንስ አፈወርቅ የኖሩበት ዘመን ለባህላዊው ሙዚቃ የነበረውን ቦታ፣ የሚከወንበትን አውድ፣ ሙዚቃ ተጫዋቾቹ ሙያቸውን የሚቀስሙበት፣ የሚያሳድጉበት ይትበሀል ምን ነበር! የሚለውን አጠቃላይ ዘመኑን የሚያሳይ ነው::

የቃላዊ ታሪክ አጥኚ የሆኑ ፎክሎሪስቶች በግለሰቦች ትውስታ፣ የህይወት ልምድ ቀረጻና በቡድኖች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። የሚሰበሰቡ መረጃዎችም ቀደም ሲል ገነው ያልወጡ በቃል ብቻ ሲተላለፉ የቆዩ አተያዮችና ሀሳቦች ናቸው። ይህም የሚያስፈልገው ቀደም ሲል የነበሩ መረጃዎችን ለማጠናከርና የታዩትን ክፍተቶች ለመሙላት ነው (Ritchie, 2003,19)። በዚህ ጥናትም እስካሁን ስለ ዋሽንት ተጫዋቹ ዮሐንስ አፈወርቅ ከራሳቸውም ሆነ በዘመኑ አብረዋቸው ከነበሩ ሌሎች ባለሙያዎች ስለ ስራዎቻቸው የተናገሩት በትውስታ ነው። በጋዜጣ፣ በመጽሄት እንዲሁም በመገናኛ ብዙሀን የተዘገቡ እና ለዚህ ጥናት ዋቢ የሆኑ የዮሐንስ ታሪክም ትውስታን መሠረት አድርጎ 'እንዲህ አድርጌያለሁ! እንዲህ አድርጎ ነበር" በሚሉ የተሳታፊ ምልከታ እና ከህይወት ልምድ የተገኘ የቃል መረጃ ነው። በዮሐንስ አፈወርቅ የህይወት ልምድና ስራዎቻቸው ላይ የተጠና ጥናት ባለመኖሩ ቃላዊ መረጃዎችን መዝግቦ ማቆየት ወደፊት ሊጻፍ ይችላል ተብሎ ለሚጠበቀው የኢትዮጵያ ሙዚቃ በተለይ ዋሽንት ጨዋታ ይህ ጥናት ትልቅ ግብአት ነው።

ቃላዊ ታሪክ የማህበረሰብ ታሪክን የሚገነባና በአሁኑና በመጪው ትውልድ መካከል ያለ ድልድይ ነው። ለቃላዊ ታሪክ ፋይዳ ያላቸው ትውስታዎችና ግለሰባዊ የህይወት ገጠመኞች የሚገኙበት ዘዴ ቃለመጠይቅ ነው። የቃላዊ ታሪክ ጥናት ዋና ምንጭ የሆነው ትውስታን መሰብሰብና የተሰበሰበውን መረጃ ቀርፆ ማስቀመጥን ያካትታል (Brown et al., 1998)።

በቃላዊ ታሪክና በማህበረሰብ መካከል ያለው ግንኙነት እጅግ የጠበቀ ነው። ምክንያቱም የቃላዊ ታሪክ ጥናት በመጥፋት ላይ ያለን የማህበረሰብ የጋራ ታሪክ ማቆያ ነው። የጠፉትን በመጥፋት አደጋ ውስጥ ያሉትን ቅርሶች በቃላዊ ታሪክ ቃለመጠይቅ የነበረውን ለማስታወስ፣ ለማያውቀው ለማሳወቅ ያግዛል። የቃላዊ ታሪክ የመረጃ ምንጮች፣ መረጃ አቀባዮች በህይወት ዘመናቸው የአሁን የሚሏቸው፣

ወቅታዊና የተሳተፉባቸው ድርጊቶች፣ የሰሙዋቸውና በአይን ያዩዋቸው ክንውኖች ትውስታዎች ፎቶዎች ናቸው። መረጃውን መውሰድ ያለባቸው በሚጠናው ጉዳይ ለምሳሌ ድርጊቶች ከሆኑ በዚያ ላይ የተሳተፉትን እና/ ወይም የቅርብ ተሳትፎ ከነበራቸው ምንጮች ነው። ይህ አይነቱ ቃለ መጠይቅ በጽሁፍ ካለው መረጃ ጋር ይነጻጸራል (Vansina, 1985)።

## የጥናቱ ዘዴ

የቃላዊ ታሪክ መረጃ አቀባዮች በቃል ሲተላለፉ የቆዩትን የማህበረሰብ መገለጫዎችን የሚያውቁ፣ የሚያስታውሱ እንዲሁም መግለጽ የሚችሉ ጉዳዩ የሚመለከ ታቸው የማህበረሰቡ አባላት መሆን አለባቸው።

ለቃላዊ ታሪክ መረጃ ሲሰበሰብ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና የቡድን ውይይት ነው። ከመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ባልተናነሰ የሰነድ ፍተሻ አስተዋጽዎ አለው። ዋንኛ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የሆነው ቃለ መጠይቅ ሲሆን አይነቱም ጥልቅ ቃለመጠይቅ (Indepth interview) ነው። ቃላዊ ታሪክን፣ ቃላዊ ታሪክ ሊያሰኘው የሚችለው በጠያቂና በተጠያቂ መካከል የሚካሄዱት ጥያቄና መልሶች በወጉ መደራጀት መቻል ነው። ስለዚህ ቃላዊ ታሪክ ሲጠና በወጉ የተዘጋጁና የተደራጁ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች ያስፈልጋሉ(Ritchie, 2003)።

የተለያዩ ዲሲፒሊኖች በቃለመጠይቅ መረጃ ሲሰበስቡ የሚከተሏቸው መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የቃላዊ ታሪክ መረጃ ሰብሳቢ ግን የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች ከሚፈልገው ግብ ውጪ እንዳይወጣ አቅጣጫ ሰጪ በማድረግ፣ ቃለመጠይቁን አስቀድሞ በማዘጋጀት፣ በባለሙያ አስገምግሞ ከተጠያቂው ትውስታዎች መካከል የሚፈልገውን መረጃ የማውጣት አቅም ያለው ሊሆን ይገባል (Ritchie, 2003)።

በዚሁ መሠረት ለዚህ ጥናት የሰነድ ምንጮቹ የዮሐንስ አፈወርቅ ቃለመጠይቅ እንዲሁም በቅርብ የሚያውቋቸው ሙያቸውን በተመለከተም በየመድረኩ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት ዋሽንት ሲጫወቱ አብረው የነበሩ ባለሙያዎች የጻፏቸው

የተናገሯቸው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ለዚህ ጥናት በግብአትነት አገልግለዋል። ሌላው ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታወስ ያለበት ዮሐንስ አፈወርቅ ህይወት እና ስራዎቻቸው ላይ የተጠና ቀደምት ጥናት ወይም ዝምድና ያላቸው ጥናቶችን ክለሳ ማድረግ ቢፈለግም የተሰራ ስራ ባለመኖሩ ያሉት የጋዜጣ እና የድህረ ገጾች መረጃ በግብአትነት አገልግለዋል።

# የጥናቱ ትንተና

## ባለዋሽንቱ ዮሐንስ አፈወርቅ ማንነት እና ሙያዊ አበርክቶ

በዚህ ክፍል የዮሐንስ አፈወርቅን የህይወት ታሪክ በተለይ ከሙያው ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ነው። ሌላው ዋሽንት ለመዳው ከየት ተጀመረ እንዴትስ ዳበረ የሚለው ሁለተኛው እና የጥናቱ አብይ ጭብጥ ይሆናል።

### የዮሃንስ አፈወርቅ ትውልድና እድገት

ዮሐንስ አፈወርቅ ጀንበሬ ሀምሌ 2009 ዓ.ም. ለዚህ ጥናት ግብአት የሆነውን መረጃ ሲሰጡ "እድሜዬ 71 ነው" ብለው ነበር። የተወለዱት ታህሳስ 3 ቀን 1938 ዓ.ም. ጎጃም አቸፈር ተክለሃይማኖት ነው[1]። ወላጅ እናታቸው ወለላ ተገኝ አባታቸው ቄስ አፈወርቅ ጀንበሬ ይባላሉ። ቄስ አፈወርቅ ጀንበሬ ልጃቸው ዮሐንስ አርአያቸውን እንዲከተሉ ወደቤተክርስቲያን ሲሄዱ ልጃቸውን አስከትለው ነበር። "አባቴ የቄስ ትምህርት እንድማር፣ ቤተክርስቲያን በመሄድ ከበሮ እንድመታ ያደርጉ ነበር።"[2]

ዮሐንስ አፈወርቅ ግን አባታቸው ከሚመኙላቸው እና እንዲለማመዱት ከፈለጉት የሃይማኖት ትምህርት እንዲሁም ከበሮ መምታት ይልቅ አባታቸው የማይወዱት ዋሽንት ጨዋታ ቀልባቸውን ሳበው። ከሸንበቆ [ዋሽንት] ጨዋታ የተዋወቁት በትውልድ ቀዬአቸው አብረዋቸው ጥጃና ፍየል ሲጠብቁ በእድሜ ከፍ ይሉ ከነበሩት እረኞች ነው። ስምንት አመት ገደማ ሲሆናቸው እሳቸውም ሸንበቆ መንፋት

[1]ጎጃም አዊ ዞን በፋግታ ሊኮማ ወረዳ ልዩ ስሙ በክታ ከምትባል ቦታ ተወለዱ።

[2] ዮሐንስ አፈወርቅ አዲስ አበባ፣ ቃለመጠይቅ ሰኔ 26 2009ዓ.ም።

ጀመሩ። ከእረኝነት ውጭ ሰፈር ውስጥ ሲውሉ አባታቸው እንዳይሰሟቸው ተደብቀው ሽንበቆ ይነፉ ነበር። "...እኔ አባቴን እንድተካ እንጂ እንድዘፍን አይፈለግም።"[3]

ዮሐንስ እድሜያቸው አስራዎቹን መቁጠር ሳይጀምር የዋሽንት ጨዋታ መውደዳቸውን ያስተዋሉት አባታቸው 'አንተ ዘር አሰዳቢ ነህ! እንዴት ሽንበቆ ትነፋለህ' ብለው ይቆጧቸው እንደነበር ያስታውሳሉ።

> ሽንበቆ ማሰናዳት አልችልም ሰው የሰራውን ግን እጫወትበ ታለሁ። ቤት ወስጄም የሳር ክዳን በሆነው ቤታችን ጣራ ስር እደብቀዋለሁ። ምክንያቱም እህቶቼ ካዩ ለአባቴ ሽንበቆ ነፋ ብለው ይነግሩታል፤ አባቴም ሽንበቆውን ይሰባብርሩብኛል። 'ዋሽንት መንፋት' የሚለውን የሰማሁት እዚህ አዲስ አበባ መጥቼ ነው። ቤተሰቦቼ ቤት ሆኜ የባእድ ሰርግ ሲኖር እጫወታለሁ። የዘመድ ሰርግ ላይ አልጫወትም።[4]

ዮሐንስ አፈወርቅ ቤተሰቦቻቸውን ትተው ወደአዲስ አበባ ለመሄድ ሰበብ የሆናቸውን ሲገልጹ "ወደ አዲስ አበባ የመጣሁት ዋሽንት ስጫወት ያዩኝ የአካባቢው ነዋሪዎች አዲስ አበባ ብትሄድ! ሲሉኝ ልቤ ሸፈተ" በማለት ያለከልካይ ዋሽንት ለመጫወት በስም ብቻ ወደሚያውቋት አዲስ አበባ ለመሄድ ተመኙ። ዮሐንስ አፈወርቅ ወደ አዲስ አበባ ሂድ! ሂድ! የሚላቸውን ስሜት እውን ለማድረግ በቅድሚያ ወላጆቻቸው "ይሂይስ" ብለው ያወጡላቸውን "ዮሐንስ" በሚለው ስም ለወጡ። ጓደኞቻቸውም በአዲሱ ስማቸው እንዲጠሯቸው አደረጉ። በ16 አመታቸው በ1955ዓ.ም፡-

> አንድ ማለዳ ለገበያ አዲስ ኪዳን [ቅዳም] ሄጄ መኪና አየሁ። መኪናውን ሰዎች ከበው ያዩታል። ባለመኪናውን ዳንግላ ውሰዱኝ አልኳቸው እሺ ብለው አሳፈሩኝ። ዳንግላ ስንደርስ ውረድ ቢሉኝ፤ አልወርድም አልኳቸው። ለምን አትወርድም ሲሉኝ 'እናትና አባት የለኝም፤ እዚህ እረኛ ያደርጉኛል' ብዬ አስተዛዝኜ ለመንኳቸው። የመኪናው ባለቤት አቶ ነዋይ ወልደማሪያም አንድ ቤት እንዳድር ብር ከፈሉልኝ። የተከፈላቸው ሴት ቤት መደብ ላይ አደርኩ። በማግስቱ ማለዳ

[3] ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ ሰኔ 28 2009 ዓም።

[4] ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ ሰኔ 28 2009 ዓም።

ያደርኩበት ቤት አቶ ነዋይ መጡ፤ እግራቸው ላይ ወድቄ አዲስ አበባ ወሰዱኝ ብዬ ለመንኳቸው። ...አዲስ አበባ አቶ ነዋይ ቤት ሰንደርስ ይዘው የመጡትን ማር ተሸክሜ ወደቤት አስገባሁ፣ ሰራተኛቸው ወ/ሮ አልታዬ ሙሉ እንደ እንግዳ አስተናገደችኝ። የአቶ ነዋይ ልጆችም እንደ ብርቅ ሲያዩኝ፤ እኔም የከተማ ልጅ አላውቅም አያቸዋለሁ።[5]

አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ የትውልድ ቀዬአቸውን የለቀቁት የቤተሰብ ፈቃድ ሳይጠይቁ እንዲያውም ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ የባለመኪናውን ይሁንታ ለማግኘት ሲሉ 'ቤተሰብ የለኝም' ብለው ስለነበር በአቶ ነዋይ ቤት ከቤተሰቡ አባላት እንደ አንዱ በመሆን ኑሯቸውን ቀጠሉ። በአንደኛው ቀን እቃ ለመግዛት ተልከው ሲሄዱ ይወዷት የነበረችዋን ሸንበቆ የማግኛ አጋጣሚ ፈጠረላቸው። "አንድ ቀን እንደልማዴ ተልኬ ስሄድ የሰፈር ዘበኛ ሸንበቆ ይዞ አየሁት። ተቀብዬ ተጫወትኩ። ባለ ሸንበቆው በአግራሞት ይመለከተኝ ነበር። በሌላው ቀን ያችን ሸንበቆ ይገዘበት ጠፋሁ።[6]

ዮሐንስ አፈወርቅ በልጅነት እድሜ ዘመድ የሚሉት ሳይኖር በስም ብቻ ወደሚያውቋት አዲስ አበባ መጥተው ሲኖሩ የተለያዩ ውጣ ወረዶችን አልፈዋል። በዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ ለእሳቸው እንደመልካም አጋጣሚ የሚቆጥሩት ሀገር ቤት ሆነው ይጫወቷት የነበረችውን ሸንበቆ አግኝተው እንደልባቸው መጫወታቸውን ነው። ለዮሐንስ አፈወርቅ ዋሽንት ጨዋታ ለመዝናናት ወይም የግል ስሜታቸውን ለማርካት ብቻ የሚጫወቱት ሳይሆን እንደሙያ፤ ባለሙያ እንደስራ መተዳደሪያቸው የሆነው በአጋጣሚ ነው። በእሳቸው እምነት ደግሞ "እግዚአብሄር እንጀራህ ይሁን ብሎኝ ነው!" በሚለው ያምናሉ።

## "ዋሽንት ጓደኛዬ የሆነው ገንዘብ ለማግኘት ነው[7]"

አዲስ አበባ በጥገኝነት በሚኖሩበት ከሰፈር ልጆች ይጣሉ የነበሩት ዮሐንስ በዋሽንት በሚያሰሙት ጣእመ ዜማ አማካይነት

---

[5]ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ ባህር ዳር ሰኔ 10/ 2009 ዓ.ም።

[6] ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ ሰኔ/ 28 2009 ዓ.ም።

[7].ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ ሀምሌ 17/ 2009 ዓ.ም።

ተወዳጅ ሆኑ። ከወዳጅነት ባለፈ ልጆቹ በዋሽንቱ ድምጽ ከመማረካቸው የተነሳ ዮሐንስን ማክበር፣ ማጫወት እንዲያውም ሳንቲም መስጠት፤ ሳንቡሳና ሻይ መጋበዝ ጀመሩ። ዮሐንስም በጨዋታው ደስታን ማግኘት በልጆቹ ሽልማት በመበረታታት የዘወትር ተግባራቸው ልጆቹን በዋሽንት ማዝናናት ሆነ። አንድ ቀን እንደተለመደው ለሰፈር ልጆች ዋሽንት እየተጫወቱ አንድ ሰው ወደ ትልቅ ጠጅ ቤት አብረው እንዲሄዱ ጋበዛቸው፤ ሄዱ፡፡ ጠጅ ቤቱ “እማሆይ ጠጅ ቤት” ይባል ነበር። ዮሐንስም የሚወዱትን ዋሽንት ሲጫወቱ ጠጅ ጠጪዎቹን ያዝናኑ ነበር። ይህም እየተደጋገመ የሰፈር ልጆችን ማዝናናቱ ወደ ጠጅ ቤት ተዘዋወረ፤ የህም የየእለት ተግባራቸው ሆነ። በዋሽንቱ ዜማ የሚዝናናው ታዳሚም የገንዝብ ሽልማት ይሰጣቸው ጀመር። የሽልማቱ ሳንቲም እየበዛ በእጅ ወይም በኪስ ይከተትላቸው የነበረው በሳህን እየተሰበሰበ ይሰጣቸው ጀመር::

ዮሐንስም ዋሽንት በመጫወት ከመደሰት ባሻገር መተዳደሪያቸው ከጠጅ ጠጪዎች የሚያገኙት የገንዘብ ሽልማት ሆነ። ይህን ሲገልጹ “ዋሽንቴን ይዤ መጀመሪያ እማሆይ ጠጅ ቤት፤ ከዚያም ብርጭቆ ጠጅ ቤት ገባሁ[8]።” በጠጅ ቤት በየምሽቱ ለጠጪዎች የዋሽንት ዜማ ማሰማት ቋሚ ስራቸው አደረጉት። በዚሁ አጋጣሚ ዮሐንስ በተመሳሳይ ሙያ ላይ ከተሰማራው ጅግሶ በዳሶ ጋር ተገናኙ። ጅግሶ የትውፊታዊ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች ሲሆን እሱም ሙያው ከበሮ መምታት ነበር። ጅግሶ ከከበሮ በተጨማሪ የጅምላስቲክ ስፖርት ያውቅ ስለነበረ በሰውነት እንቅስቃሴው ጭምር ጠጅ ጠጪዎችን ያዝናናል። በዋሽንት፣ ከበሮ እና በጅምናስቲክ ስፖርት ሁለቱ ባለሙያ በጥምረት ጠጪዎችን ማዝናናት፣ ጠጪዎችም ለተዝናኖቱ የሚሰጡት ሽልማት ዮሐንስ አፈወርቅን እና ጅግሶ በዳሶን አጣመራቸው። ከዚህም በላይ ወዳጅ ሆነው ውሎ አዳራቸው በአንድ ላይ ሆነ።

[8].መሀል መርካቶ አቶ ዘሪሁን የሚባሉ ጠጅ ቤት ነበራቸው። የጠጅ ቤቱ ስም ብርጭቆ ጠጅ ቤት ይባላል። ብርጭቆ ጠጅ ቤት የተባለው ሌላው ጠጅ ቤት በብርሌ ሲጠጣ እዚህ ግን በብርጭቆ ስለሚጠጣ ነው(ቃለ-መጠይቅ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አዲስ አበባ መስከረም 2010ዓ.ም)።

እማሆይ ጠጅ ቤት በሳምንቱ መጀመሪያ የተለመደ ተግባራቸውን ሊከውኑ ተገኝተው ነበር። ሆኖም አንዱ የጠጅ ቤት ወዳጃቸው ወደሌላኛው ጠጅ ቤት ይዟቸው ሄደ። ጠጅ ቤቱ መርካቶ አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ነበር። ዮሐንስ በዚህ ጠጅ ቤት እንደተለመደው ዋሽንት ሲጫወቱ አመሹ። ከታዳሚዎቹ መካከል አንድ የፖሊስ መኮንን ነበሩ። የዮሐንስን የዋሽንት አጨዋወት በማድነቅ ሙያቸውን እንዲያበለጽጉ ወደ ፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋሙ ገብተው ተጨማሪ የሙዚቃ መሳሪያ ሙያ እንዲሰለጥኑ ጠየቋቸው። ዮሐንስም በፖሊስ መኮንኑ ሀሳብ ተስማምተውና ለተደረገላቸው ግብዣ አመስግነው ወደ ማሰልጠኛው ገቡ።

## ከአማተር ወደ ሰለጠነ ባለሙያ ጉዞ

ዮሐንስ አፈወርቅ በጠጅ ቤት ባገኟቸው ጋባዣቸው አማካይነት ትውፊታ ዊ ከሆነው የዋሽንት ጨዋታ በተጨማ ዘመናዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ስልጠና ወደሚያገኙበት ተቋም ገቡ። የጠጅ ቤት ስራቸውም ሆነ ተከራይተው የሚኖሩበትን ቤት ሙሉ በሙሉ ለቀው ማሰልጠኛ ገቡ። በዚያ ይማሩ የነበረውን የሙዚቃ መሳሪያ ዘመናዊ ስለመሆኑ እንጂ እውቂያ አልነበራቸውም። ከዚያ በፊትም መደበኛ ት/ቤት ገብተው አልተማሩም።

> በፖሊስ ማሰልጠኛው የሙዚቃ መሳሪያ ተመደብን። ከኖታ (ሶልፊት) ጀምሮ እንሸመድ ዳለን፤ ፍሉቱና ዋሽንቱ አያያዙ ስለሚለያይ፣ ተቃራኒ ሆኖ ተቀየረብኝ። ...ሁለት አመት ደህና እንደሰራሁ ከተማ መዋል ጀመርኩ። እሁድ እሁድ ፈቃድ ስላለን ከማሰልጠኛው እንወጣለን በዚህ አጋጣሚ የማላውቀውን ዳንስ ቤት ተለማመድኩ። በፊት አይቼ አላውቅም፣ የልጅነት ነገር ሆኖ እሱ እየሳበኝ በትምህርት ቀን ሳይፈቀድልኝ እየወጣሁ ቀሪ አበዛሁ። ስወጣ ስገባ 'ቻርጅ' የሚባል ተጽፎ ይቀርባል። ቀሪ ሳበዛ ከማሰልጠኛው ተባረርኩ። ስባረር ለጊዜው ደስ አለኝ።[9]

የወታደር ቤት የሆነው ማሰልጠኛ ለዮሐንስ ቀለብ እና መኝታ እንዲሁም የኪስ ገንዘብ በወር አስራ አምስት ብር ይሰጣቸው

[9]ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ ሀምሌ 17/ 2009 ዓ.ም።

ነበር። ሆኖም ከፖሊስ ማሰልጠኛው ሲባረሩ ይህን ሁሉ አጡ። ያስቀመጡት ገንዘብ አልነበራቸውም። ወደማሰልጠኛው ከመግባታቸው በፊት የተከራዩትን ቤት ስለለቀቁ መግቢያ አጡ። የማሰልጠኛው ጥብቅ ቁጥጥር አሰልችቷቸው ስለነበር በመባረራቸው ቢደሰቱም የእለት መጠጊያ የሚሆን ገንዘብ፣ ቤት ወይም ዘመድ ስላልነበራቸው ለችግር ተዳረጉ። ይህንን ወቅት ሲያስታውሱ "…ስወጣ የማድርበት ቤት ስላልነበረኝ መርካቶ ጣና የገበያ አዳራሽ መካከል አደርኩ። ምንም ልጅ ብሆን ያቺን ምቾት ማሰብ ነበረብኝ፣ ተቀጣሁ።[10]"

ዮሐንስ አፈወርቅ ለእለት ጉርስ የሚሆን ስራ ፍለጋ በመርካቶ ለቀናት ያገኙትን የጉልበት ስራ መስራት ጀመሩ። ከጓደኛቸው ጅግሶ ጋር ወደ ማሰልጠኛ ከገቡ በኋላ የተለያዩ ቢሆንም ዳግም ተገናኙ። በመካከሉ ለሁለት አመት ያህል የሰለጠኑበትን ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ሳይሰሩበት እንደገና ሸንበቆ ፈልገው ዋሽንት አዘጋጁ። በዚህች ዋሽንትም ከጅግሶ ጋር ዳግም በጋራ በመሆን በየምሽቱ በጠጅ ቤቶች እየተዘዋወሩ የዋሽንት ጨዋታቸውን እንደ አዲስ ጀመሩ። ጓደኝነታቸውም ከቀድሞው የጠነከረ ሆነ።

ዮሐንስ አፈወርቅ የጠጅ ቤት የዋሽንት ተጫዋችነታቸው እየገነነ ሄደ። ጅግሶም ከበሮ እና የጅምናስቲክ ስፖርቱን ከዋሽንቱ እየቀናጀ ሙያቸው የበለጠ እየዳበረ ሄደ። ከጎጃም ቀጥሎ ሀገራቸው የሆነው አዲስ አበባ ነበር። ሆኖም በዚሁ ዋሽንታቸው ተማምነው ከጅግሶ ጋር ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አመሩ። መጀመሪያ የሄዱት ወደ ጅግሶ የትውልድ ሀገር ሲዳማ ነበር። "ሲዳማ ስንደርስ ኦርኬስትራ መጣ ተብሎ በክብር ተቀበሉን።" እንደ አዲስ አበባ ሁሉ የዋሽንት መጫወቻ መድርካቸው ጠጅ ቤት ነበር። " …ሲዳማ ሄደን ጠጅ ቤት እየገባን የምንወደውን ዘፈን ዜማ ለጠጅ ጠጪው እናሰማለን በዋሽንት የተጫወትኩት ዘፈን የአለማየሁ እሸቴን፣ የጋሽ ታምራትን (ታምሜ ተኝቼ) ነበር።[11] ዮሐንስ አፈወርቅ ከጅግሶ ጋር ወደ አዲስ አበባ በመመለስ አራት

[10]ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ መስከረም 2010 ዓ.ም።

[11]ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ መስከረም 2010 ዓ.ም።

ኪሎ አካባቢ ቤት ተከራይተው በአንድ ቤት ተዳብለው መኖር ጀመሩ።

## ከጠጅ ቤት ወደ ተደራጀ የሙዚቃ ቡድን አባልነት

ዮሐንስ ከጅግሶ ጋር በየምሽቱ በየመጠጥ ቤቱ እየዞሩ ጠጪዎችን በማዝናናት የሚያገኙት የገንዘብ ሽልማት ብቸኛው የገቢ ምንጫቸው እንደሆነ ቀጠለ። አንድ ቀን ጅግሶ ብቻውን በጠጅ ቤት ከበሮውን ከተለየ የሰውነት እንቅስቃሴው ጋር አዋህዶ ጠጪውን ሲያዝናና ከታዳሚዎቹ አንዱ ግለሰብ የጅግሶን ጨዋታ በማድነቅ ወደ አንድ ተቋም ለስራ ጋበዘው።

> አንድ ቀን እኔ አሞኝ ጅግሶ ብቻውን ሄደ። በአጋጣሚ ጅግሶ አክሮባት ሲሰራ ጋሽ ተስፋዬ አይቶት 'ተስፋዬ ለማ[12] ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርሲቲ' የሚል አድራሻ የተጻፈበት ወረቀት ሰጠው። በማግስቱ አብረን አድራሻው ላይ በተገለጸው መሠረ ት ወደ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርሲቲ ሄድን። ተስፋዬ ለማን ከማግኘታችን በፊት አልማዝ[13] አየችን። እኔን ስለምታውቀኝ በመደነቅ ስሜት አጠገቧ ለነበሩት 'ዋሽንት የሚጫወተው መጣ' ስትል እኔ አፈር አልኩ። ጋሽ ተስፋዬ እሷ ያለችውን ሰምቶ የተጋበዝንበትን የጅግሶን ጉዳይ ሳያሳውቀን እኔን ወደ ቢሮው ጋበዘኝ። ... 'አራቱን ቅኝት[14]' እንድጫወት አዘዘኝ፤ ዋሽንቴን በኪሴ ይዤ ስለነበር እኔ ቅኝት[15] መሆናቸውን አላውቅም ግን ሰው ሲጫወታቸው ሰምቼ እወደው ስለነበረ ይዤዋለሁ፤ አሳምሬ ተጫወትኩ። ስጨርስ 'ከዛሬ ጀምሮ ተቀጥረሀል የመስሪያቤታችን

---

[12]በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (ዛሬ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የሆነው) ዩኒቨርሲቲ ኪነጥበባት ወቴያትር [Creative Arts Center] ውስጥ ይቀጠራል። ዲሬክተሩ ታዋቂው የቴያትር ባለሙያና መምህር አቶ ተስፋዬ ገሠሠ ነበር፣ማዕከሉ ኦርኬስትራ ኢትዮጵያን በሥሩ ይዟል፡፡

[13]አልማዝ ጌታቸው የወላይትኛ ዘፈኖችን በእንቅስቃሴ ጭምር የምትጫወት ነበረች። በኋላ ዮሐንስ አፈወርቅም የገቡበት የኦርኬስትራ ኢትዮጵያ አባል ሆና ትሰራ እንደነበር ይገልጻሉ(ተስፋዬ 2005፣ 228፤ Timekehet, 2018, 10)።

[14] አራቱ ቅኝት ማለት ባቲ፣ አንቺ ሆዬ፣አንባሰልን እና ትዝታ ናቸው።

[15]"...በአራት የተመደቡ ቅኝቶች ትዝታ(የቀድሞ ስሙ ወሎ)ባቲ፣ አንባሰልና አንቺ ሆዬ ለእኔ ናቸው። እነዚህ አራት ቅኝቶች የተገኙት ከወሎ ክፍለሀገር ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ በጊዜው የነበሩት መሰንቆ ተጫዋቾች የተሰበሰቡት ከወሎ ስለነበረ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ። ለምሳሌ ማሲንቆ ተጫዋቾቹ ከጎንደር ቢሆኑ ኖሮ የቅኝቶቹ ስሞች ሌላ ሊሆኑ ይችሉ ነበር(ተስፋዬ፣ 2005፣ 120)።"

ባልደረባ ነህ!’ አለኝ።...እኔም ደንግጬ ጅግሶ ካልተቀጠረ እኔ አልቀጠርም አልኩ! ...ተስፋዬ ‘በጀት ስለሌለን አንተ ጀምር እና እሱን ደግሞ እንቀጥረዋለን’ አለኝ፣ በወር በሰላሳ አምስት ብር ደሞዝ ተቀጠርኩ። በዚያን ጊዜ በሰባት ብር ከሀምሳ ሳንቲም አንድ ኩንታል ጤፍ ይገዛ ስለነበር ትልቅ ብር ነው። ...በኋላ ጅግሶም ተቀጠረ[16]።

ዮሐንስ አፈወርቅ የዋሽንት ጨዋታ ሙያቸውን አይቶ የቀጠራቸው ተቋም በ1960 ዓ.ም በባህል ሙዚቃ ጥሩ እውቀት ያላቸውን ሙዚቀኞች በማሰባሰብ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርሲቲ ቤተ ኪነጥበባት ወቲያትር[17] ስር በሙዚቃ ባለሙያ[18] የተቋቋመ ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ ነው። ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ተቋም እንዲቀጠሩ ያደረጋቸው የሚጫወቱት የሙዚቃ መሳሪያ ነው። “በጊዜው ከነበሩት የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴና የሀገር ፍቅር ቲያትር ቤቶች ለየት የሚያደርገው ቡድኑ ያቀፋቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች በሌሎች የሙዚቃ ቡድኖች ዘንድ የሌሉ መሆናቸው ነው” (ተስፋዬ, 2005, p.223)።

በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ የባለሙያዎች ስልጠና እና የሙዚቃ ቡድን ወይም ተቋም ምስረታው በግለሰቦች ጥረት እና በጎ ፈቃድ ላይ ስለሆነ እድገቱም ውድቀቱም በግለሰቦች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነበር። በተለይ የባህል የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች በተፈጥሮ ተሰጥዎ እንዳላቸው የሚያውቁት በባለሙያ ተገምግመው ሳይሆን በታዳሚው ህዝብ ግብረ መልስ፤ ሙያውም የሚዳብረው በግል ጥረታቸው ነው። ግለሰቡ በግል ጥረቱ ሙያውን ያዳብራል፤ ባለሙያም ይባላል[19]።ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ የሙዚቃ ቡድን መሪ የነበሩት እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ ያሉ የባህል ሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች ቡድኑ ሲመሰረት እንደነበሩ በኋላም የባህል ሙዚቃ

[16] ዮሐንስ ቃለመጠይቅ አዲስ አበባ መስከረም 2010ዓ.ም።

[17]የኢትዮጵያ ሙዚቃ በዩንቨርሲቲ ደረጃ እስኪቋቋም ድረስ በባህል ሙዚቃ ጥሩ እውቀት ያላቸውን ሙዚቀኞች በማሰባሰብ በ1960ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩንቨርሲቲ ቤተ ኪነጥበብ ወቴያትርን ስር ተቋቋመ(ተስፋዬ፣ 2005፣ 222)።

[18]የዚህ ቡድን መስራች በትውልድ ግብጻዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆኑት ከፍተኛ የሙዚቃ ባለሙያ ፕሮፌሰር ሐሊምኤልድሐብ ነበሩ (ተስፋዬ፣ 2005፣ 222)።

[19] ባህልና ስፖርት ሚኒስተር። የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሙያተኞች ማህበር ድርጅታዊ አሰራር የአባላቱ የኑሮ ሁኔታ የተመለከተ ጥናት። ጥር 1973 (ያልታተመ)።

መሳሪያ ተጫዋቾቹ ቁጥራቸው እየቀነሰ ሄዶ እንዲያውም ...የመጨረሻው የእንቢልታ ተጫዋቾች የነበሩት የኦርኬስትራ ኢትዮጵያ አባላት ነበሩ (ተስፋዬ, 2005)።

ኪነጥበብ ወቲያትር በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርሲቲ ውስጥ የገቡት ለባለሙያዎቹ የሙዚቃ ልምምድ ቋሚ መለማመጃ ቦታ ለማግኘት እንጂ ባለሙያዎቹ ወይም የሙዚቃ ቡድኑ በዩንቨርሲቲው የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ እንደባለሙያ ተካተው አልነበረም። ቡድኑ ቋሚ የገቢ ምንጭ ሳይኖረው ቀርቶ በነበረበት ለመቀጠል አልቻለም። ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ ለባህል የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች የሶስት ወር ደሞዝ እና የሚጫወቱበትን የባህል የሙዚቃ መሳሪያ ለባለሙያዎቹ በመስጠት[20] ቋሚ መገናኛና የእኛ የሚሉት መሰብሰቢያ ቦታ በማጣቱ አሰናበታቸው። ባለሙያዎቹ ተቋሙ ቢያሰናብታቸውም አልተለያዩም። ዮሐንስ ይህን ትውስታቸውን ሲገልጹ፡

> በአምስት ብር ሺ ሰማኒያ (የዛሬው ራስ አንባ ሆቴል) አካባቢ ቤት ተከራይተን እቃውን አስቀመጥን። መገናኘት ስንፈልግ ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን እንገናኛለን።በጋሼ ተስፋዬ ሰርግ ሲኖር ይነግረናል። ቻርለስም እንዲሁ ስራ ሲኖር ለጋሼ ተስፋዬ ይነግርና እንጫወታለን። በተጨማሪም የዛሬው ሲፒኤ ስልክ ሰጥተናል፣ ሲደወልልን እንሰራለን። ሰርግ ቤት ስንሄድ ለአራት አንድ ታክሲ በአንድ ብር ኮንትራት እንይዝና የተጠራንበት ሰርግ ቤት እንሄዳለን። አንዳንዴ ጓደኞቼ ለስራ ሄደን ልንጫወት ስንል ማሲንቆ ወይም ክራር ረስተው ይመጣሉ። እኔ ግን ዋሽንቴን ኪሴ ስለምከት አልረሳም።[21]

ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ የሚለውን ስማቸውን ይዘው ስራ በተገኘበት አጋጣሚ በጋራ እየሰሩ፣ አንዳንዶቹም የተለያየ አጋጣሚ እየፈለጉ በውጭም በሀገር ውስጥም በተለያየ መድረክ ላይ የቡድኑ ስራ እንዲታወቅና እንዳይበተን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ይህን በተመለከተ በወቅቱ የኦርኬስትራው መሪ የነበሩት ተስፋዬ ለማ

[20]ለባህል ሙዚቃ ተጫዋቾች የተሰጣቸው ለምሳሌ ከበሮ፣ ማሲንቆ፣ ክራር ይገኙበታል። ዮሐንስ አፈወርቅ ዋሽንት የግላቸው እና በየሄዱበት ከኪሳቸው የማይለያቸው በመሆኑ አልተሰጣቸውም፤ ዮሐንስ ቃለመጠይቅ)

[21]ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ ዐዲስ አበባ፣ ሀምሌ 2009ዓ.ም።

በአንድ ወቅት በወቅቱ ስለነበረው የሙዚቃ ቡድን ተጠይቀው የሚከተለውን ብለዋል።

> ሺ ሰማንያ ተብሎ በሚጠራው ሠፈር ቤት ተከራይተን በሠርግ፣ እንዲሁም ቱሪስቶች ሲመጡ እንሠራ ነበር። የማልዘነጋው ወንድሜ፣ ወዳጄ የሆነው ቻርልስ ሳተን ያኔ ለሰላም ጓድ [Peace Core] ተልዕኮ መጥቶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢንጂነሪንግ ኮሌጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ያስተምር ነበር። ታዲያ የዚህ ኦርኬስትራ መቅረት አሳዝኖት "በእኔ ምትክ ሌላ ሰው መድቡና እኔ ድጋፍ አሰባሳቢ [Fund raiser] ሆኜ አስተዳድረዋለሁ፣ ከመፍረስ አድነዋለሁ" ብሎ አለቃውን ጠየቀና ተፈቀደለት።ከዚያ ከልዩ ልዩ ኤምባሲዎች ጋር በመፃፃፍ የነፃነት ወይም ብሔራዊ በዓላቸው ሲሆን እንዲጋብዙን አግባባቸው፡፡በተለይ ከአሜሪካ ኤምባሲ ብዙ ጥሪዎች አመጣልን። ኦርኬስትራው ከመፈራረስ ዳነ። ቻርልስ በዚህ አላበቃም።አሜሪካ መጥቶ መሰንቆውን እየተጫወተ 'ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ የሚባል የጥንት ሙዚቀኞችን የያዘ ቡድን ሊፈርስ ነው፣ የዓለም ሃብት ነውና እርዱኝ' ብሎ ወደ ሶስት ሺህ የአሜሪካን ዶላር ሰብስቦ ላከልን። ያን ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የኑሮው ሁኔታ በጣም ግሩም ነበር። ስምንት ብር ምን የመሰለ በግ ይገዛል።እንደውም ቆዳው ሲሸጥ ስጋውን በነፃ እንደመብላት ነበር። ያ ገንዘብ በእውነቱ ለአስራ ስድስታችን ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ደሞዛችንን ሊሸፍን ቻለ(ታዛ መጽሂት)።

ዮሐንስ አፈወርቅ ተቋሙ ቢፈርስም ከሌሎች መሰል ባለሙያዎች ጋር ቁርኝት ፈጥረው በዋሽንት ጨዋታ መዝናናት ለሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች እንዲጋብዙዋቸው መንገድ ከፈተላቸው። በተለያዩ የግለሰብ ወይም የቤተሰብ እና የቡድኖችን ደስታ ለማድመቅ በተጠሩበት እየተዘዋወሩ ዋሽንት መጫወታቸውን ቋሚ እና ብቸኛው መተዳደሪያቸው ሆኖ ቀጠሉ። ወደፊት እንደምናየው በተለያዩ ትያትር ቤቶች በዋሽንት ተጫዋችነት እንዲቀጠሩ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገር ወክለው ዋሽንት እንዲጫወቱ ኦኬስትራ ኢትዮጵያ መሠረት ሆኗቸዋል። ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያን ከፍ የሚያደርግ እና የበለጠ የሚያስተዋውቅ አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር። ለምሳሌ በደራሲ ተስፋዬ ለማ የተደረሰ "እኛም አለን ሙዚቃ ስሜት የሚያነቃ" በሚለው ግጥም የሙዚቃ

መሳሪያ የሚተዋወቅበት ወቅት ነበር፡፡ ይህ ማስታወቂያ መሰል ሙዚቃ እንደ ዮሐንስ ያሉትን ባለሙያዎች ተፈላጊነታቸው እየጨመረ እንዲመጣ አድርጓቸዋል፡፡ በ1961 ዓ.ም ዘመን መለወጫ በአል ከክቡር ዘበኛ ጦር ጋር ተሰልፈው እንደ ሀገር ትልቅ ስራ ሰሩ::

በወቅቱ በየአመቱ የዘመን መለወጫ ዋዜማ ላይ አዳዲስ ዜማዎችን በማቅረብ ልዩ ልዩ የሙዚቃ ክፍሎች የሚሳተፉበት የሙዚቃ ውድድር ይደረግ ነበር። ተፋላሚዎቹ በአንድ በኩል የሀገር ፍቅር ማኅበር፣ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ኦርኬስትራ፣ ብሄራዊ ቲያትር፣ …የክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ፣ የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲው ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ፣ ምድር ጦር ይግኙበታል። በእነዚህ ቡድኖች መካከል ከፍተኛ የሆነ የስራ ፉክክር ይታያል።…ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ባህላዊና ዘመናዊ ዘፈኑ፣ ውዝዋዜው 'ተአምር' ሊባል የሚችል ነው።..ይህ ሁሉ የባለሙያዎች ፉክክር ሙያውን ለማሳደግ…የእገሌ ቡድን አንደኛ ወጣ ለመባል ነው (የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር, 2002, pp.28-29, p.175)።

ከኦርኬስትራ ኢትዮጵያ አባላት መካከል ዮሐንስ አፈወርቅ አንዱ ነበሩ። በዚህ ውድድር ላይ በወቅቱ ስሙ ገኖ የሚነሳው እና ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎችን ለምሳሌ እነጥላሁን ገሰሰ ያሉበት የሙዚቃ ቡድኖች የሚፎካከሩበት ነበረ። ዮሐንስ አፈወርቅም በእንደዚህ አይነቱ ውድድር ላይ በመሳተፋቸው በሙያቸው ከሚያስታውሷቸው መልካም ገጠመኞች አንዱ ነው።ተስፋዬ ለማ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ መጽሀፋቸው ከኦኬስትራ ኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች በስም ከሚጠቅሷቸው መካከል አንዱ ዮሐንስ አፈወርቅ ሲሆኑ በኦርኬስትራ ኢትዮጵያ ታሪክን ባቀረቡበት ክፍል፤ ስለዮሐንስ አፈወርቅ በቡድን እንዲሁም በግል ፎቷቸውን ጭምር በማካተት በሚከተለው መልኩ ገልጸዋቸዋል። "በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ በዋሽንት አጨዋወት እጅግ የተደነቀው ዮሐንስ አፈወርቅ ትሑት፣ ሙያውን አፍቃሪና ከሰዎች ተግባቢም ነው። የኢትዮጵያ የባህል ሙዚቃ ቡድን በተዘዋወረባቸው ሀገሮች ሁሉ በሙያው ታላቅ አገልግሎት የሰጠ ግሩም ሙዚቀኛ ነው" (ተስፋዬ, 2005, p.225)። በማለት ስለሙያቸው በባለሙያ ምስክርነት አግኝተዋል።

## የዮሐንስ አፈወርቅ ዋሽንት አጀብ፣ ለወጋየሁ ንጋቱ ፍቅር እስከ መቃብር ትረካ

ዮሐንስ ከአሜሪካ መልስ በ1962 ዓ.ም. ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ እየሰሩ የገንዘብ ችግር ኪነጥበብ ወቲያትር ከተቀላቀሉ ከሶስት አመት በኋላ ትዳር መሰረትኩ፡፡ ባለቤቴ የመጀመሪያ ልጃችንን ልትወልድ ተቃርባለች፣ ዘመን መለወጫ ደርሷል፣ ባዶዬን ነኝ ገንዘብ የለኝም።"[22] ይህንን ችግራቸውን ለተስፋዬ ለማ ሲነግሯቸው በዋሽንታቸው እንዴት ገንዘብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ሀሳብ ሰጧቸው። ሀሳቡም በወቅቱ ከተለያዩ የሙዚቃ ባለሙያዎች ሙዚቃቸውን በድምጽ እያስቀረ ገንዘብ ይሰጥ ወደነበረው ተቋም እንዲሄዱ ያደረጋቸው ነበር። በተስፋዬ ምክር መሠረት ዮሐንስ በወቅቱ ማስታወቂያ ሚኒስቴር በመባል ወደ ሚታወቀው በመሄድ ዋሽንት ሲጫወቱ ድምጹ እንዲቀረጽ ጠየቁ፣ ተፈቀደላቸው። "በ1962 እና 1963ዓ.ም. በጠየኩት መሠረት የቻልኩትን ያህል ዋሽንት ተጫወትኩ ተቀረጸ፣ እኔም ገንዘብ አገኘሁ ችግሬን ተወጣሁ"።

የግለሰቦችን ሙዚቃ ገዝቶ የማስቀመጥ ባህል የተጀመረው በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስቴር የሬዲዮ የሙዚቃ ክፍል ሀላፊ በነበሩት አቶ ፀጋዬ ደባልቄ ባመጡት ሀሳብ ነበረ። በዚሁ ዘመን የነበሩ የሙዚቃ ስራዎች ቅርስ ሆነው እንዲቀመጡ የተደረገበት ጊዜ ነው። ከዚያን በፊት በነበረው የሀገሪቱ ሬዲዮ ጣቢያ ዘፈን ለአድማጩ ለማሰማት ሲፈለግ ባለሙያው ሬድዮ ጣቢያው ድረስ በመሄድ ሙዚቃውን ለህዝብ ያቀርብ ነበር። በወቅቱ የሙዚቃ ባለሙያዎች ቡድን የነበሩት፤ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቲያትር፣ በክብር ዘበኛ የምድር ጦርን በፖሊስ ሰራዊት፣ በሀገር ፍቅር፣ በኦርኬስትራ ኢትዮጵያ እንዲሁም በባህል የሙዚቃ መሳሪያ የሚጫወቱ ግለሰቦች ነበሩ። የእነዚህ ባለሙያዎች ስራ ወይም ሙዚቃ በድምጽ ተቀርጾ በወቅቱ ተከማችቷል። ይህ በወቅቱ የተቀረጸ ሙዚቃ "አርካይቭ" ሊሆን እንደሚችል ምኞታቸውን ጠቁመዋል (ተስፋዬ, 2005, p.27)።

በተለይ ለዮሐንስን የዋሽንት ዜማቸው መቀረፁ ስራቸውን ህዝብ ደጋግሞ እንዲሰማው እንዲያውቃቸው የማድረግ እድል

[22] ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ መስከረም 2010 ዓ.ም።

ፈጥሮላቸዋል። በዚህን ወቅት ስለተቀረጸው የዜማው ብዛት ዮሐንስ ባያስታውሱም አዲስ ዘመን ጋዜጣ የዮሐንስን ህልፈት አስመልክቶ ባወጣው ጽሁፍ "...ከአብዮቱ በፊት የማስታወቂያ ሚኒስቴር ከኦርኬስትራዎችም ሆነ ከቴአትር ቤቶች ሙዚቃዎችን ይገዛ ነበር። ከመቶ በላይ የሚሆኑ የዋሽንቱ ንጉሥ ዮሐንስ አፈወርቅ ስራዎችም የተቀረጹት እንዲህ ባለ ሁኔታ ነው (አዲስ ዘመን, 2011)" ሲል የዜማውን ብዛት ጠቁሟል።

ዮሐንስ አፈወርቅ በ1963 ዓ.ም.ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት በዋሽንት ተጫዋችነት ተቀጠሩ። የተቀጠሩትም ነው። ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት እንዲሰሩ ሲቀጠሩ በወር በአርባ ብር ደመወዝ ሲሆን ሙያቸውን የበለጠ እንዲያዳብሩ እንደረዳቸው ተናግረዋል። ዮሐንስ አፈወርቅ ምንም እንኳዋን ኦርኬስትራን ትተው ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ቢቀጠሩም በደመወዙ ማነስ ቅሬታ አድሮባቸው በሁለተኛ አመታቸው 1965ዓ.ም. ወደ ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ ተመለሱ[23]።

ዮሐንስ አፈወርቅ በሀገር ውስጥ እውቅናን ያሰጣቸው የተለያዩ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን ሰርተዋል። የታዋቂ ዘፋኞችን ዘፈን በዋሽንታቸው አጅበዋል። ለምሳሌ ዛሬ ድረስ በድምጽና በምስል ተቀርጾ ለአድማጭ ተመልካች የሚቀርበው የጥላሁን ገሰሰ "እዩዋት ስትናፍቀኝ" ዜማን ቀይ ጃኖ ለብሰው በዋሽንት አጅበዋል። ይህንን ስራ በሰሩበትና በመሰል የስራ አጋጣሚዎች በተለይ እንደነ ጥላሁን ገሠሠ የታወቁ ዘፋኞችን በዋሽንትም ሆነ በመሰል የሙዚቃ መሳሪያ ለማጀብ ይሽቀዳደሙ እንደነበር ዮሐንስ ያስታውሳሉ[24]።

በህዝብ ዘንድ በተለይ በወቅቱ በነበረው ሬዲዮ ጣቢያ ዮሐንስን ያስተዋወቃቸው የዋሽንት ዜማ ለሀዘን መግለጫ ወይም ለመሰል ድባብ ዜና ማወጃ ማጀቢያ ሆኖ መቅረቡ ሌላው አጋጣሚ ነው። በ1966 ዓ.ም በወቅቱ ወሎ ክፍለ ሀገር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተከሰተ ድርቅ የሀዘን ዜና ሲነገር ማጀቢያ ሆኖ ሀዘኑ በሰው ልብ እና አእምሮ ገዝፎ እንዲሰማ ያደርግ የነበረው የዮሐንስ አፈወርቅ የዋሽንት ዜማ እንደነበር ይጠቁማሉ (አዲስ ዘመን, 2011)።

[23]ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ መስከረም 2010 ዓ.ም።

[24] ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ መስከረም 2010 ዓ.ም።

የፍቅር እስከ መቃብር ረዥም ልብወለድ ተራኪ የነበረው ወጋየሁ ንጋቱ የዮሐንስን የዋሽንት ዜማ ለትረካው ማጀቢያ ሲመርጥ በሬዲዮ ጣቢያው ከሚገኘው የድምጽ ክምችት መካከል የወደደውን ወይም ለፈለገው አላማ የተሻለ ያለውን መረጠ እንጂ ዮሐንስ ለዚህ ትረካ ማጀቢያ ብለው የተጫወቱት አይደለም።

> በ1973 ዓ.ም. በአል ለማክበር መስቀል አደባባይ እኔ እና ወጋየሁ ንጋቱ በተለያየ አቅጣጫ ስራችንን ለማቅረብ ተገኘን። በዚህ ዝግጅት ላይ ወጋየሁ ንጋቱ የእኔን የተቀረጸ ዋሽንት ዜማ አቀረበ። ከጨረሰ በኋላ ጠጋ ብዬ 'ይሄ ዋሽንት የማን እንደሆነ አውቀሀል?' ብዬ ጠየኩት። ወጋየሁ ቆጣ ብሎ 'የሬዲዮ ጣቢያው ነዋ!' አለኝ። 'አይ የእኔ ነው' ስለው 'ውሸታም' ብሎ ተቆጣኝ። ወጋየሁ ንጋቱ በዚያው እለት ሬዲዮ ጣቢያ ሂዶ ያቀረበው የዋሽንት ዜማ የማን እንደሆነ ሲያረጋግጥ የተመዘገበው በእኔ ስም መሆኑን አወቀ። ወጋየሁ በወቅቱ እሰራበት ወደነበረው ማዘጋጃ ቤት መጥቶ አቅፎ ሳመኝ። አደነቀኝ፣ አመሰገነኝ። [25]

ዮሐንስ አፈወርቅን ከብዙዎች ያስተዋወቃቸው የፍቅር እስከ መቃብር ትረካ ማጀቢያ ከአመታት በፊት (በ1962 እና በ1963 ዓ.ም.) ገንዘብ ለማግኘት ብለው ማስታወቂያ ሚኒስቴር ካስቀረጹት የዋሽንት ዜማ መካከል አንዱ ነው። ሆኖም ትረካው ተደጋግሞ በሬድዮ ለሶስተኛ ጊዜ ሲቀርብ ወደ ሬድዮ ጣቢያ ሂደው እንደነበረ ያስታውሳሉ።

> የፍቅር እስከ መቃብር ትረካ ሶስተኛ ዙር ሲተላለፍ 'እልፍኝ ባህሩ ቆርቆሮ ፋብሪካ' ስፖንሰር ማድረጋቸውን ስሰማ ሬዲዮ ጣቢያ ሄድኩ። ስሄድ ደጀኔ ጥላሁንን አገኘሁት። ድርጅቱ ለሬድዮ ጣቢያው 'ማቴሪያል ሰጥተዋል እንጂ ምንም ገንዘብ የለንም' ካለ በኋላ ወዲያው ለፋብሪካው ባለቤት ስልክ ደወሎ ፋብሪካቸው የሚተዋወቅበት የዋሽንት ዜማ ማጀቢያ የሰራው ባለሙያ መጥቷል አላቸው። "የተጫወተው በህይወት አለእንዴ!" ብለው በመገረም ወዲያው ሬዲዮ ጣቢያ መጡ። ሲያዩኝ ያውቁኛል 'አንተ ነህ እንዴ!' ብለው በመገረም 'ተጫወትልኝ' አሉኝ። እዚያው ዋሽንቱን ከኪሴ

[25] ቃለመጠይቅ ዮሐንስ አፈወርቅ ሀምሌ 2009ዓሸም።

> አውጥቼ ተጫወትኩላቸው።የተጫወትኩት ተቀረጸ የሳቸውም አስተያየት ተካቶ እንደገና ተቀረጸ።[26]

በዚህ መልኩ በሬድዮ ጣቢያ ለህዝብ በሚተላለፉ የተለያዩ ፕሮግራሞች ዋሽንትም ሆነ ሌሎች ሙዚቃዎች ይቀርባሉ። ሆኖም ስራው በመቅረቡ ባለሙያው ምንም አይነት ጥቅማ ጥቅም አያገኝም።[27]

የፍቅር እስከመቃብር ማጀቢያው የዮሐንስ አፈወርቅ ዋሽንት በ2007 ዓ.ም እንደገና በሙዚቃ አድማጩ ህዝብ ዘንድ እንዲሰማ ሌላ አጋጣሚ ተፈጥሯል። ይሄውም በቴውድሮስ ካሳሁን “ማር እስከ ጧፍ” የሚለው ሙዚቃ ይዘት መነሻ ሀሳብ ከሀዲስ አለማየሁ ልብወለድ ድርሰት ፍቅር እስከመቃብር የተወሰደ ነው። ከዚሁ ጋር አያይዞ የወጋየሁ ንጋቱን ትረካ ቀንጭቦ ሲጠቀም የዮሐንስ አፈወርቅ ዋሽንትም ይሰማል። ይህን በተመለከተ ለዚህ ጥናት ቃለመጠይቅ ሲደረግላቸው “ቴዎድሮስ ካሳሁን የእኔን ዋሽንት ለሙዚቃው ማጀቢያ ስለተጠቀመበት አመስግኖኛል፤ ለእኔ ምስጋና በቂዬ ነው” ሲሉ ተናግረው ነበር።

በሀገር ውስጥ በተለይ በደርግ ዘመን ለእናት ሀገር ጥሪ ዝግጅት ኤርትራን ጨምሮ በተለያዩ የሰሜኑ የሀገራችን አካባቢዎች ሀገር የጣለችባቸውን ግዴታ ተወጥተዋል። ሌላው ዮሐንስ አፈወርቅ ባይታወቁበትም የእኔ ነበር የሚሉት የዋሽንት ዜማ በብዙዎች የሚሰማው የኢትዮጵያ አየር መንገድ መለያ የሆነው የዋሽንት ዜማ ነው። “ምንም እንኩዋን በሙላቱ አስታጥቄ ስም ቢመዘገብም የኢትዮጵያ አየር መንገድ እራሱን ለማስተዋወቅ የሚያሰማው የዋሽንት ድምጽ የእኔ ነው” በማለት ይገልጻሉ። ዮሐንስ አፈወርቅ ዘግይተውም ቢሆን “የእኔ ነው” በማለት ይመለከተዋል ወዳሉት የኢትዮጵያ አየር መንገድ በመሄድ መጠየቃቸውን ይናገራሉ።

---

[26]ቃለመጠይቅ ዮሐንስ አፈወርቅ ሰኔ ባህርዳር 2009ዓ.ም።

[27]ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ በ2013 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ ሲቀርብ ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በተመለከተ ዳዊት ይፍሩ በወቅቱ እሳቸውም ይሳተፉበት የነበረውን የሙዚቃ መድረክ በቅርብ የሚያውቁትን መረጃ ዋቢ በማድረግ ለባለሙያው ምንም አይነት ክፍያ እንደማይከፈል ልምዳቸውን አክለው ተናግረዋል።

ሆኖም አየር መንገዱ ዜማውን ድርጅቱን ለማስተዋወቅ ሲል ከሙላቱ አስታጥቄ መግዛቱን ለዚህም ተገቢው ክፍያ ተከፍሎ ባለቤትነቱም በሙላቱ አስታጥቄ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ እንደተነገራቸው ለዚህ ጥናት መረጃ ሲሰጡ ገልጸዋል። በተጨማሪም ይህንኑ በተመለከተ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በወጣ ጽሁፍ ላይ ከዮሐንስ አፈወርቅ ስራዎች መካከል አንዱ እንደነበር "በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ኢትዮጵያዊነታችንን በድምፅ ምናብ አግዝፎ እየሳለ እንካችሁ ያለን" በማለት ገልጾታል (አዲስ ዘመን፣ የካቲት 24 2011)።[28]

ሌላው ስራቸው የተለያዩ ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎችን በዋሽንት ዜማቸው ማጀብ ነበር። ለምሳሌ ጥላሁን ገሠሠ፣ ታምራት ሞላ፣ አለማየሁ እሸቴ፣ ተፈራ ካሳ፣ ታደሰ አለሙ፣ ሒሩት በቀለ፣ ለማ ገብረሕይወት፣ ጸሀዬ ዮሐንስ እንዲሁም ሙላቱ አስታጥቄ ይገኙበታል።

## የዮሐንስ አፈወርቅ ዋሽንት በዓለም ሀገራት መድረክ

በ1961ዓ.ም.ዮሐንስ እና ሌሎችም ወደ አሜሪካ የሄዱት ቻርልስ በአሜሪካ ለኦርኬስትራ ኢትዮጵያ ባመቻቸው ጉዞ ሲሆን ይህን አስመልክቶ ዮሐንስ የሚከተለውን ብለዋል።የ

> አሜሪካ የሄድኩት በኦርኬስትራ ኢትዮጵያ ነው። የተለማመድነው አራት ኪሎ ሲሆን የተጫወትነው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ብቻ ነበረ። በተለይ እንቢልታ የተጫወተውን ሁለተኛው ጀምስ ብራዎን ብለው አድንቀውት ነበር። ግጥሞቹ እየተጻፉ ይበተናሉ፣ እነ ከበደ ወ/ሚካኤል ደግሞ እየተቀባበሉ ይዘፍናሉ። በየከተማው እየዞርን የመጨረሻውን ስራ ዋሽንግተን ዲሲ አቀረብን።[29]ች

በ1964ዓ.ም ኬንያ ሁለት ጊዜ ሱዳን አንድ ጊዜ ዋሽንት ለመጫወት መሄዳቸውን ያስታውሳሉ። ዮሐንስ ከተሳተፉባቸው ስራዎች መካከል ትልቅ የሚባለው በወቅቱ የተለያዩ ታዋቂ ኢትዮጵያዊያን አርቲስቶች በተለያዩ የዓለም ሀገራት የተሳተፉበት የሕዝብ ለሕዝብ መድረክ የተባለው ስራ ተጠቃሽ ነው። በኢትዮጵያ

[28]ይህ ዜማ በታዋቂው ኢትዮጵያዊ የኢትዮ ጃዝ ሙዚቃ ባለሙያ ሙላቱ አስታጥቄ ስም ተመዝግቦ ይገኛል።

[29]ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስአበባ፣ ጥቅምት 2010 ዓ.ም።

የሙዚቃ ታሪክ ተደጋግሞ የሚነሳው ትልቁ ስራ እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች ይገልጻሉ (ተስፋዬ, 2005; የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር, 2002)።

የሕዝብ ለህዝብን መድረክ በወቅቱ አሉ የተባሉ የሙዚቃ ባለሙያዎች[30] እንዲሁም ከየብሄረሰቡ የተውጣጡ የየብሄረሰቡ የሙዚቃ አዋቂዎች የተሳተፉበት መድረክ ነበር። የዚህ መድረክ መነሻ ሀሳብ እና አላማን በተመለከተ በወቅቱ በአስተባባሪነት በቡድን መሪነት እና በተለያየ ደረጃ የተሳተፉ ግለሰቦች የነበረውን አጠቃላይ አውድ በተለያየ አጋጣሚ ይገልጻሉ።

> የህዝብ ለህዝብ የባህል ቡድን የተጠነሰሰው በዚያን ወቅት የሻዕቢያ የሙዚቃ ቡድን በሮምና በሚላኖ ለሚኖሩ ኤርትራውያን የቅስቀሳና መዝናኛ ዝግጅት አቅርቦ ነበር። ዝግጅቱም ኤርትራዊያንን 'ለአመጽ የሚያነሳሳና በኢትዮጵያም ላይ ጥላቻ የሚያሳድር ነበር' ይባላል። በወቅቱ በሮም የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት አቶ ተስፋዬ አብዲ ኢትዮጵያዊያንን ለመካስ አንድ የኪነት ቡድን እንዲላክላቸው ለኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ጥያቄ ያቀርባሉ።

በዚህ መልኩ በወቅቱ የነበሩ የመንግስት ባለስልጣናት ሙዚቃን ለፖለቲካ አላማ ማሳኪያ እንደ ትልቅ መሳሪያ ለመገልገል ሀሳቡን አነሱ። ሌላው የሕዝብ ለሕዝብ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የባህል ዘመቻ የተደገሰው እና የተተገበረበት ዋንኛ አላማ በሀገሪቱ ላይ ለደረሰው ረሀብና ቸነፈር የረዱትን የዓለም ሀገራት ለማመስገን ነው። በተጨማሪም ኢትዮጵያን ለማያውቀው የዓለም ህብረተሰብ ለማስተዋወቅ፤ እንዲሁም በውጭ ሀገር ይገኙ የነበሩትን ኢትዮጵያዊያን የአገር ፍቅር ስሜት ለመቀስቀስና የባህል ተሀድሶ ለመስጠት ነበር። በወቅቱ በውጭ ይኖሩ ከነበሩ ኢትዮጵያዊያን የመንግስት ተቃዋሚዎች መድረኩን ወዳልታሰበ አቅጣጫ እንዳይሄድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ለማድረግ ወስነው ኮሚቴ አቋቋሙ[31]። በኮሎኔል

[30]በሕዝብ ለሕዝብ መድረክ ከተሳተፉት መካከል ክቡር ዶክተር ጥላሁን ገሠሠ ሀገርን ወክለው በዓለም ላይ ከሰሯቸው ስራዎች መካከል ቀዳሚ መሆኑን የህይወት ታሪካቸውን በሚዘክረው መጽሀፍ ውስጥ ተጠቁሟል (የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር 2002)።

[31]የኮሚቴው ሰብሳቢ መንግስቱ ኃይለማሪያም፣ ምክትል የርእዮተ አለም መምሪያ ሀላፊ አቶ ሽመልስ ማዘንጊያ። ለዝግጅቱ ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታ አንድ ሚልየን

መንግስቱ ኃይለማሪያም ወሳኝነት የቱሪዝም ኮሚሽን፣ የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድና የባህል ሚኒስቴር ሀላፊዎች የሚገኙበት ኮሚቴ ተቋቋመ።በጊዜው ከተሳተፉትና የህዝብ ለህዝብ ኢትዮጵያ የማስታወቂያና የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ የነበሩት ማዕረጉ በዛብህ የዘመቻውን የጉዞ ጥንቅር የያዘ ዘገባ ዋቢ አድርገው ይጠቁማሉ (የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር፣ 2002፡ 183)።ይህም ህዝብ ለህዝብ የተባለው መድረክ ዮሐንስ አፈወርቅ ከሌሎች ሙዚቀኞች ጋር በመሆን ሀገርን ወክለው በተለያዩ የዓለም ሀገራት በመዘዋወር የዋሽንት ጨዋታን ያስተዋወቁበት ትልቁ መድረክ ነበር። በአርቲስት ሙላቱ አስታጥቄ አቀናባሪነት የተለያዩ የሙዚቃ ባለሙያዎችን የያዘ ቡድን ተቋቋመ፡፡ በዚህ መሰረት ጌታመሳይ አበበ መስንቆ፣ አሊያስ አረጋ በክራር፣ ኮት ሁጁሉ በቤዝ ጊታር፣ ተካ ጉልማ በከበሮ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ በዋሽንት በመሆን ነበር (አዲስ ዘመን, 2011)።

ሕዝብ ለሕዝብ ኢትዮጵያ የሚለውን መድረክ በትልቅ ታሪካዊ የኪነጥበብ ስራ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው እንዲሁም ዮሐንስ አፈወርቅም ለሀገር ሰራሁት ከሚሉት በቀዳሚነት የሚጠቅሱት ቢሆንም አብሮ በወቅቱ የነበረውን አስቸጋሪ ገጠመኝ አይዘነጉትም።

> የህዝብ ለህዝብ ጉዞ ብዙ መከራ ታይቶበታል፤ ትልቅ ስራም የሰራሁበት ነው። በጄኔቫ ጉዞ የማልረሳው ፎቅ ባለው አውቶቡስ የባህል ልብስ ለብሰን እየተጓዝን ሳለ በድንገት መሀል ከተማ ላይ ውረዱ እና እዚህ ተጫወቱ አሉን። የሀገራችን ሰዎች ሲያዩን በጣም ተሸማቀቁ። ፖሊስ መጣ በኋላ በስንት መከራ ሳንታሰር ቀረን። ፈረንሳይ ፓሪስ ደግሞ የተገጣጠበ ቤት አሳድረው ወደ ጄኔቫ እንድንሄድ ተደረገ። የተወዛዋዥ ሳጥን አስረሀንድ ነበረ። እሱ ተጭኖ ፓሪስ አካባቢ ጉዞ ጀመርን ስንሄድ ውለን አደርን። የባህል ኮሚሽን ሚኒስቴር አቶ ሀብተስላሴ ታፈሰ ቋንቋ ስለሚችሉ አስተርጓሚ ሆነው አብረውን ነበሩ። ቦርደር ላይ ስንደርስ

ተኩል ብር በላይ ወጪ ሆነ። የየብሄረሰቡ አባላትና ጌጣጌጦች ባማረ ሁኔታ ለማሟላት ተችሏል። በ1980 ዓ.ም. ዓለምን በዞረው የሕዝብ ለሕዝብ የኪነት ቡድን የመጨረሻ ዝግጅት ወቅት ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያምና የቅርብ ረዳቶቻቸው ለሶስት ቀናት ያህል ከሌላ ስራቸው ርቀው አመራር ሰጥተውበታል (ተስፋዬ፣ 2005፣ 280-281፡317)።

ፖሊስ ለሁለት ሰአት ያህል አስቆመን። ፓስፖርት አሳይተን በጭቅጭቅ አለፍን። እሱን ጨርሰን ወደ ራሻ ሄድን። ራሻ ደግሞ ቋንቋውን አንችልም። ከፕሌን ወርደን እቃ ስንጠብቅ ይሰድቡን ነበር፣ ሆቴል ሄደን ስናርፍም ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች እዚህ እንዴት ይሰራሉ ብለው በመጮህ ተቃወሙ[32]። እንደምንም ብለን እዚያም ሰርተን ጨርሰን ወደ ሆቴላችን ተመለስን። የያዝነውን አስረሀንድ ሳጥን ልብስና እቃዎች የባቡሩ ፉርጎ አይችልም ተብሎ ትንሽ እቃና ልብሳችንን ይዘን ሄድን። ስንደርስ አልጋ ጠፋ በአንድ ክፍል ውስጥ ዘጠኝ፣ዘጠኝ ሆነን ተጨንቀን አደርን።በማግስቱ ኢትዮጵያ ኤንባሲ ሄደን ስብሰባ ነበረን በኋላ እዚያው ኢንባሲ ግቢ ውስጥ ከየቦታው ለተሰባሰቡ ኢትዮጵያዊ ተማሪዎች አቀረብንላቸው። የመጨረሻውን ስራ ያቀረብነው ግሪክ ነበር። ተቃዋሚ ሁሉ ተሰልፎ ሀገሩ ሙቀት ስለሆነ የሚቀርበው ሜዳ ላይ ነበር። በመካከሉ አንዱ ነጭ ተመታ በዚያው አበቃን። በፊት ሲሰድቡን የነበሩት ኢትዮጵያዊያን ተቃዋሚዎች ስራችንን ሲያዩ አልቅሰዋል። እኔ እንኩዋ እንባዬ አፌ እየገባ መጫወት አቅቶኝ ነበር።ከኢትዮጵያ ስንነሳ እቅዳችን ሰባት ወር ለመቆየት ነበር። ሆኖም በአራት ወራችን ተመለስን።[33]

ሌሎችም በህዝብ ለህዝብ መድረክ የተሳተፉ ባለሙያዎች ዮሐንስ አፈወርቅ የነበረውን ድባብ የገለጹበትን በተለይ በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ሥርአት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ተቃውሟቸውን ለመግለጽ መድረኩን እንደ መልካም አጋጣሚ መጠቀማቸው የተሳተፉትን ባለሙያዎች ለተለያየ እንግልት ዳርጓቸዋል። ሕዝብ ለሕዝብ ኢትዮጵያ አገራዊ ተልእኮውን ለመወጣት የሚያስችል የሶስት ወራት ልምምድ በብሔራዊ ሸንጎ የመሰብሰቢያ አዳራሽ አድርጎ ነበር። የቡድን መሪዎችን ጨምሮ 56 አባላት ነበሩት። ዝግጅቱ ከኢጣልያ ዋና ከተማ ሮም ጀምሮ በአስራ ስምንት የአውሮፓና የአሜሪካ ከተሞች

---

[32] ዮሐንስ አፈወርቅ ተቃዋሚ ያሏቸው በወቅቱ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። የህዝብ ለህዝብ ኢትዮጵያ ቡድኖችን ሰበብ በማድረግ፤ በጊዜው በነበረው የደርግ ስርአት ላይ የነበራቸውን ተቃውሞ ለመግለፅ ነው። "በየከተማው ተቃዋሚ ወገኖች ከሚያሳዩት የገሀድ ተቃውሞ ሰልፍ ሌላ እውቅ አርቲስቶችን በማስከዳት የጉዞው ተልእኮ እንዲከሽፍ ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል። ...አርቲስቶቹን አባብለው ለማስቀረት ከመሞከር በላይ በተለይ ክቡር ዶክተር ጥላሁን ገሰሰ፣ ማህሙድ አህመድ እና ብዙነሽ በቀለን አፍነው በመውሰድ ለማስከዳት ሞክረዋል (የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር 2002፣ 184-185)።"

[33]ቃለመጠይቅ፤ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አዲስ አበባ፣ ሀምሌ 2009 ዓ.ም።

በመዞር፣ ጄኔቫ ላይ አጠናቆ በ118ኛ ቀኑ ወደ እናት ሀገሩ ተመለሰ (የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር, 2002)።

ኢትዮጵያን ወክለው በዓለም መድረክ ላይ ከተገኙት መካከል የዮሐንስን አስተዋጽዎ እና የዋሽንት ጨዋታ ልዩ ችሎታ የህዝብ ለህዝብ ዝግጅት መሪና ዮሐንስን በቅርበት የሚያውቋቸው ሲገልጹ፤ "ሁሉም ሙዚቀኛ ሁለት ሁለት በመሆን አንዱ ሲደክመው ሌላኛው እንዲያግዝ ሲደረግ አርቲስት ዮሐንስ አፈወርቅ ግን ብቻውን ከአንድ ሰዓት በላይ በማይቋረጠው ሙዚቃ በብቃት ቅኝት እየሰጠ ያገለገለ የዋሽንት ንጉሥ ነው" (አዲስ ዘመን, 2011)፡፡

ከኢትዮጵያ ውጭ በቡድን ሆነው ህዝብ ለህዝብ ላይ እንደተሳተፉት ሁሉ በሌላም ጊዜ በተለያዩ የዓለም ሀገራት ተዘዋውረው የዋሽንት ሙዚቃን አቅርበዋል። ለምሳሌ ናይጄርያ፣ ሱዳን፣ ግብጽ፣ አሜሪካ፣ ጣልያንና ፈረንሳይ ይገኙበታል።

## የዮሐንስ አፈወርቅ የዋሽንት አጨዋወት ብቃት በባለሙያ ዐይን

ስለ ዮሐንስ አፈወርቅ ዋሽንት አጨዋወት ብቃት ከዋሽንቱ ጠባይ ጋር በማያያዝ የተለያዩ ባለሙያዎች ሙያዊ አስተያየት ሰጥተዋል። ከእነዚህ መካከል ህዝብ ለህዝብ ላይ በቡድን መሪነት ዮሐንስ አፈወርቅን በቅርበት የሚያውቋቸው ጸሐፊ ተውኔት እና ገጣሚ አያልነህ ሙላቱ ዮሐንስን እንደሚከተለው ገልጸዋቸዋል።

> ዮሐንስ ዝም ብሎ ዋሽንት ብቻ የሚጫወት ሙዚቀኛ አይደለም፤ በሚጫወትበት ወቅት ዐይንም ቀልብም የሚስብ እንቅስቃሴ ስለሚያደርግ የተመልካች ትኩረት በሙሉ እርሱ ላይ ስለሚሆን ሌሎች ሙዚቀኞችንና ተወዛዋገሮችን እስከ መሸፈን ይደርስ የነበረ ነው። የሚገርመው ዋሽንት መጫወት ከባድ ትንፋሽ ይፈልጋል፤ ያንን ተቋቁሞ እንቅስቃሴ መጨመሩ የተለየ ተሰጥኦ እንዳለው ያስታውቃል። ማንም ይህንን በቀላሉ ሊያደርገው አይችልም፤ዮሐንስ ግን ይህንን የታደለ ሙዚቀኛ ነበር። ፈረንጆች መጥተው ዮሐንስ አፈወርቅ ከኋላ የሚረዳው ነገር አለ እንጂ ብቻውን ይህንን ሊያደርግ አይችልም አሉኝ። የሙዚቃ ባለሙያው የተለየ ተሰጥኦ ያለውና ያለ አንዳች የሰውም ሆነ የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንደሚጫወት ነግሬያቸው በመድረክ ላይ እየተጫወተ ከጀርባው ወስጄ አሳይቻቸዋለሁ (አዲስ ዘመን የካቲት, 24, 2011)።

ዮሐንስ አፈወርቅ በባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ሙዚቀኞች አንዱ ናቸው። ከሕዝብ ለሕዝብ መድረክ ቀደም ብሎም በተለይ በኦርኬስትራ ኢትዮጵያ የነበሩ የባህል የሙዚቃ ተጫዋቾች በዓለም መድረክ በመዞር የኢትዮጵያን ባህላዊ ሙዚቃ ሲጫወቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ዘዴዎች ጭምር አድንቀው እንደጻፉ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን በስም ጭምር ዮሐንስን ይጠቅሷቸዋ (Timkihit 2018, p.11)።

ዮሐንስ አፈወርቅን በዋሽንት ጨዋታ የሚያስደንቃቸው የተለየ አጨዋወታቸው ብቻ ሳይሆን የሙዚቃ መሳሪያው በራሱ አስቸጋሪ መሆኑና ይህንን አስቸጋሪ የሙዚቃ መሳሪያ ያለእንከን መጫወት መቻላቸው ነው። የሙዚቃና ቴአትር ሙያተኛው ተስፋዬ አበበ ዋሽንት ጨዋታን አስመልክተው "ዋሽንት ከኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ትንፋሽ የሚጠይቅ ከባዱ መሳሪያ ነው። ዮሐንስ በዚህ በኩል አንቱ የተባለ ነው፤ ምትክ የለውም። …ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ በነበረ ጊዜ … ትዝታ፣ አምባሰል፣ ባቲ የኢትዮጵያ ቅኝቶችን በረቀቀ ሁኔታ ያስደምጥ ነበር።"

ዮሐንስ አስቸጋሪ የተባለውን ዋሽንት ከተለመደው አጨዋወት ባለፈ ፈጠራ አክለውበት ሰው እንዲወደው ማድረጋቸውን ሙያውን በቅርበት የሚያውቁ ግለሰቦች ይመሰክራሉ። ከእነዚህ መካከል ጌታቸው ወርቅዬ የተባለው ወጣት የዋሽንት ተጫዋች የዋሽንት አጨዋወት ከሌሎቹ የትንፋሽ መሳሪያ በተለየ አስቸጋሪ እና ማንም ሰው ያለተሰጥኦ እና ልምድ ሊጫወተው እንደማይችል በርእዮት ሚዲያ ላይ በተደረገለት ቃለመጠይቅ ገልጿል። ከዚሁ ጋር አያይዞ የተለያዩ ዋሽንት ተጫዋቾችን ስምና ስራዎቻቸውን በመግለጽና በማነጻጸር "ጋሽ ዮሐንስ የአሁኑንም የድሮውንም ዜማ የፈለግነውን የሚጫወቱልን ትልቅ የዋሽንት ባለሙያ ናቸው[34]።" በማለት ገልጿቸዋል።

ሌሎችን አስተምረዋል ወይ ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ያስተማሩት እንደሌለ ጠቁመዋል። ይህን አስምልክተው የሙዚቃ ባለሙያ የሆኑት ዳዊት "እውቀትን ስለማሸጋገር በሸገር ሬዲዮ ጣቢያ

[34]ጌታቸው ወርቅዬ፣ ርዕዮት ሚዲያ 2008፣ኢቢኤስ ቴሌቪዥን።

ዮሐንስ ተጋብዞ እኔም ባለሁበት ለማንም አላስተላለፍኩም እኔ ስሞት አብሮኝ ይቀበራል ብሎ መልሷል[35]" ሲሉ ገልጸዋል።

"በፊት ወርቅዬ መኩሪያ የሚባል ልጅ ነበረ። በኋላ ሞተ። ልጁ ጌታቸው ግን አሜሪካን ሀገር ነው። እሱም ይጫወት ነበር እኔን የሚተካኝ እሱ ነው። ሌላው ደግሞ አቡ ገብሬ ሀገር ፍቅር ያለው ዋሽንት ተጫዋች ጎበዝ ነው።" በማለት የእሳቸውን የዋሽንት አጨዋወት ስልት ይተካሉ ያሏቸውን ተናግረዋል። ዮሐንስ ይተካኛል ያሉት ዋሽንት ተጫዋችም ለዚህ ጥናት ቃለመጠይቅ ካደረግን በኋላ በሚዲያ ቀርቦ "የእኔ አጨዋወት ወደ ጋሽ ዮሐንስ ያደላል።[36]" ሲል ይህንኑ የሚያጠናክር ሀሳብ ሰጥቷል።

ዮሐንስ አፈወርቅ ከግማሽ ምእተ አመት በላይ በዋሽንት ጨዋታ ስራ ላይ ቆይተው በ1995 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ባህል አዳራሽ በጡረታ ተሰናብተዋል። በጡረታ ላይ እያሉ አጋጣሚውን ሲያገኙ ዋሽንት ይጫወቱ ነበር። ጡረታ ከወጡ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ካዛንችስ መናኸሪያ አካባቢ በሚገኘው ፊንድቃ የምሽት የባህል ሙዚቃ በሚቀርብበት ኢትዮ ከለር ከተባለ የሙዚቃ ባንድ ጋር ለሁለት አመት ገደማ ተጫውተዋል።

ይህን ያህል አመት በግልም በተለያዩ የባህላዊ ሙዚቃ ባለሙያዎችን ቀጥረው በሚያሰሩ ተቋማትም ጭምር ሲሰሩ በልምድ ያዳበሩት እውቀት በልምዳቸው ልክ ለሌሎች አላስተላለፉም። ለሌሎች የሚያስተላልፉበት አጋጣሚም በሙዚቃ ትምህርት ቤትም ይሁን ተቀጥረው በሰሩባቸው ተቋማት የተዘረጋ የአሰራር መዋቅር ባለመኖሩ እውቀታቸውን ሳያስተላልፉ ቀርተዋል። በስጋ የወለዷቸው አምስት ልጆች ቢኖራቸውም የዮሐንስን ዋሽንት የሚያነሳ ልጅ ግን አላፈሩም። የዮሐንስ አፈወርቅ ህልፈትም እንደ አንድ ግለሰብ ህልፈት ብቻ የሚታይ አይደለም። ምክንያቱም በእውቀታቸው ልክ በርካታ ባለሙያ ማፍራት ሲችሉ በተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል ሳያፈሩ በመቅረታቸው ነው።

---

[35]ዳዊት ይፍሩ፤ ይህ ጥናት ጥር 27 እና 28 በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ማንዴላ አዳራሽ በቀረበበት ወቅት የሰጡት ሀሳብ ነው።

[36]ጌታቸው ወርቅዬ፣ ርዕዮት ሚዲያ 2008፣ ኢ.ቢ.ኤስ ቴሌቪዥን።

ዮሐንስ አፈወርቅ የአራት ወንዶች እንዲሁም የአንዲት ሴት ልጅ አባት ነበሩ። ለረዥም አመታት እስከ ህልፈታቸው አዲስ አበባ መነን ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ስፔን ኢምባሲ አጠገብ ይኖሩ ነበር። ባለቤታቸው አርፈው፤ ልጆቻቸውን ያሳደጓቸው አያቶቻቸው እንደሆኑ ነግረውኛል። ህይወታቸው እስካለፈበት ድረስ ከልጃቸው ጋር ይኖሩ ነበር። ዮሐንስ አፈወርቅ የካቲት 18 ቀን 2011 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ስርዐተ ቀብራቸው በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የካቲት 19 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 9:00 ሰዓት ተፈጽሟል።

## ማጠቃለያ

ዮሐንስ በመደበኛ ትምህርት ቤት ሳይገቡ ፊደል ሳይቆጥሩ በህጻንነት እድሜ ከእረኞች የሰሙት የሸንበቆ ድምጽ ማርኳቸው እስከ ህልፈታቸው ከስልሳ አመት በላይ በዚሁ ስራቸው እየተዝናኑ፣ እያዝናኑ መተዳደሪያቸው ሆኖ ኖረዋል። ከጓደኞቻቸው በልምድ ወርሰው በድግግሞሽና በማስተዋል አዳብረው ዋሽንት ጨዋታን ከሀገር አልፈው በዓለም ዞረው ተጫውተዋል። የሀገራችንን ሙዚቃ በማጥናት "አራት ቅኝቶች አሉት" የተባለውን ዮሐንስ አልተማሩትም በቲዎሪ አያውቁትም ግን አራቱንም ቅኝት አሳምረው በተግባር ይጫወቱታል። የትውልድ መንደራቸውን ለቀው ወደአዲስ አበባ እንዲመጡ ልባቸውን ያነሳሳቸው በልጅነት እድሜያቸው ዋሽንት አጨዋወታቸውን ያስተዋለ የቀዬው ሰው ነበር። አዲስ አበባ መጥተው የሰፈር ልጆችን ሰብስቦ ዋሽንት በማሰማት የልጆችን ቀልብ ከመሳብ ጀምሮ በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ ታዋቂ በነበሩ ጠጅ ቤቶች ዋሽንታቸውን በመጫወት የብዙዎችን ልብ ገዝተዋል። ከዚህም ባለፈ እንደ ዮሐንስ ሁሉ ሌላው ከበሮ መቺ የሆነው ጅግሶንም ያገኙት ዋሽንታቸውን በሚጫወቱበት ጠጅ ቤት ነው። ዮሐንስ በጅግሶ ሰበብ የማያውቁትን ደቡብ ኢትዮጵያን በዋሽንታቸው ቃኝተዋል። ከዋሽንታቸው ውጭ ሌላ ሙያ ያልሞከሩት ዮሐንስ አፈወርቅ በየምሽት ቤቱ ስራዬ ብለው ዋሽንት ሲጫወቱ በተመለከቷቸው ግለሰቦች ምክንያት በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ የባህል ሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች በሚፈልጉ ተቋማት በመደበኛ

ሰራተኝነት ተቀጥረው ሰርተዋል። ከእነዚህ መካከል ለምሳሌ ፖሊስ ኦኬስትራ፣ ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ (እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ)። እንዲሁም ሀገር ፍቅር፣ ብሄራዊ ቲያትር፣ ማዘጋጃ ቤት ባህል ማእከል እና በመሳሰሉት ተቋማት ሰርተዋል። በእነዚህ ተቋማት አማካይነት በተለያዩ የዓለም ሀገራት ተዘዋውረው ዋሽንት በመጫወት ኢትዮጵያን አስተዋውቀዋል። በተለያዩ ዓለማት ዋሽንት ለመጫወት ከተለያዩ ስመ ጥር አርቲስቶች ጋር ዞረዋል።

ዮሐንስ አፈወርቅ በርካታ ዜማ በዋሽንት ቢጫወቱም የተጫወቱትን ያክል እውቅና አልተሰጣቸውም። ላለመታወቃቸው እንደ ምክንያት ከሚነሱት አንዱ አብዛኛው ስራቸው ተቀርጾ በወቅቱ ብቸኛ በነበረው ሬድዮ ጣቢያ መቀመጡ ነው። የትውፊታዊ ሙዚቃ መሳሪያ ጠባይ በራሱ ከሚያጅቡት ሙዚቃ ጀርባ የዋሽንቱ ድምጽ እንጂ የዮሐንስ ፎቶ ወይም ማንነት እንብዛም ያለመታየቱ ሌላው የስራቸውን ያህል ላለመታወቃቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ዮሐንስ እንደሌሎቹ የሙዚቃ ባለሙያዎች በካሴትና መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶች በስማቸው የዋሽንት ዜማን በብዛት አሳትመው ለገበያ አለማቅረባቸው ነው። ሆኖም ዮሐንስ አፈወርቅ ዘመን ተሻጋሪና ወደፊትም ትውልድ እንዲዘክራቸው የሚያደርጉ ስራዎችን እንደሰሩ በተለያየ አጋጣሚ የተቀረጹትን የዋሽንት ዜማ የሰማ የሚያስተውለው ነው።

ዮሐንስ አፈወርቅ የዋሽንት ጨዋታ ሙያቸውን ያሳደጉት በተመቻቸ መንገድ አልነበረም። በጣም አስቸጋሪ በሆነ የየእለት ኑሮን ለማሸነፍ በሚደረግ የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ነው። ከግማሽ ምእተ አመት በላይ የዋሽንት ጨዋታን ሳያቋርጡ ቢሰሩም ለጡረታ ዘመናቸው የሚሆን ጥሪት እንኳዋን ሳያፈሩ የራሴ የሚሉት ማረፊያ ጎጆ ሳይኖራቸው በስኳር ህመም በመሰቃየት ከዚህ ዓለም ተሰናብተዋል።

በዮሐንስ አፈወርቅ የህይወት ታሪክ ውስጥ በሀገራችን ኢትዮጵያ ባህላዊው ሙዚቃ በግለሰቦች ጥረት እንደኖረ እንደታወቀ እንዳደገ ማሳያ ነው። “አፍሪካ ውስጥ አንድ ሰው ሲሞት አንድ ቤተመጻህፍት የተቃጠለ ያህል ነው።" የሚለው አባባል በተግባር የዮሐንስ አፈወርቅ ሞት ማሳያ ነው። ዮሐንስን ቀጥረው ያሰሩ የነበሩት ተቋማት

የዮሐንስን በልምድ የዳበረ እውቀት ከመግዛት ውጭ በዘመናዊውም ሆነ በባህላዊው ትምህርት ቤት ገብተው ሙያቸውን ወደተሻለ ደረጃ እንዲያሳድጉ፤ እንዲሁም ሙያቸው እንደ አንድ የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ አስተማሪ ለሌሎች አስተላልፈው ተቋም መስርተው እንዲያልፉ አላገዛቸውም። የእሳቸውን አጨዋወት ለማስተማር በኖሩበት ዘመን የሙዚቃ ትምህርት ቤት፣ በተለያዩ የተሻሉ የማስተማሪያ መንገዶች ሊያስተምሩ ሲችሉ እንደዋዛ አልፈዋል።

በመጨረሻም እንደ ይሁንታ፤ እንደዚህ አይነት ባለሙያዎች ዛሬም ጥቂት ቢሆኑም አሉ። ስለዚህ እነዚህ ባለሙያዎች በህይወት እያሉ እውቀታቸውን የሚስተላልፉበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የትምህርት ተቋማት ባህል ላይ የሚሰሩ የመንግስት ተቋማት የሙዚቃ ትምህርት ቤቶች ትኩረት ሰጥተው ቢሰሩ። ሌላው ሀገር በቀሉ እውቀት ተሰጥዎን ለማወቅ፣ የእውቅት ለመዳ እና ሽግግር ስልቱ በየሙያው ተለይቶ ቢጠና ቢታወቅ ነገ ብዙ ባለሙያ ማፍራት ይቻላል። እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ ለሀገር የሚተርፍ ሀብት የሆነ እውቀት ይዘው የእለት ጉሮሮን ለመሸፈን በማያስችል ተደጋጋሚ እና መሰል ተግባር ላይ ጊዜያቸውን አጥፍተው፣ እውቀታቸውንም ይዘው ከማለፋቸው በፊት እውቀቱ ሀብት መሆኑ ታውቆ ተገቢው ክብር እውቅና ተሰጥቷቸው እውቀታቸውን በማሳደግ፣ በማስተላለፍ፣ በማባዛት ተግባር ላይ እንዲያውሉት መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት ከመንግስት ተቋማት ትክረት ያስፈልገዋል።

# ዋቢ መረጃዎች

ተስፋዬ ለማ። 2005። *የኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ* ከ1889-1983። አዲስ አበባ። ርኆቦት አታሚዎች።

ጌታቸው ወርቅዬ። 2008 ዓ.ም። ቃለመጠይቅ ርዕዮት፣ ኢ.ቢ. ኤስ ቴሌቪዥን።

አለማየሁ ገ/ሕይወት። 2010። "በባህል ሙዚቃ ረገድ የእኔ ትግል የነበረው ብሔራዊ ሙዚቃ ነው።"ታዛ መጽሄት። ደብረ ያሬድ አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር። https://taza. Debreyaredpublisher.com

አዜብ ታደሰ። 2011 ዓ.ም። የዋሽንቱ ንጉስ ዮሐንስ አፈወርቅ። አዲስ ዘመን ጋዜጣ። https: //www.press.et/ama/03.03.2019

አድማሱ አበበ። 2008። *ዲንካየዳውሮ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ*።አዲስ አበባ። ብረሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ። 2006። የአማርኛ መዝገበቃላት፤ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፕሬስ።

የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር። 2002ዓ.ም። የኢትዮጵያ የሙዚቃ ንጉስ ጥላሁን ገሠሠ (1933-200)። አዲስ አበባ። ርኆቦት አታሚዎች።

Arefaynie, F. (2019).Ethiopia's foremost washnit player, Yohannes Afework: Ethiopian Observer, Online Magazine https://www.com/2019/02/2.nen.

Donald, A. (2003). *Doing Oral History: A Practical Guide, 2nd ed.* Oxford University Press.

Timkehet,T.(2018).Ethiopian Popular Music History Chapter I PartI https://www. academia.edu/38021384/_2018.

Vansina, J. (1985). Oral Tradition as History. The University of Wisconsin press.www.dis.edu

Zenebe, B. (1987). Music in the Horn፡ Apriliminary Anlaytical Approach to the study of Ethiopian Music. Stockholm.